# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኝት ፕሮግራም፤ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ..... I
የከዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ ..... I
(EXECUTIVE SUMMERY) ..... I
ክፍል አንድ ..... 1
መግቢያ ..... 1
የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አመሰራረት ..... 1
የኢንስቲትዩቱ ራዕይ፣ ተልኮ እና ዓላማ ..... 3
የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር ..... 4
የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ..... 7
የኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ ..... 7
የኦዲቱ ዓላማ ..... 8
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..... 8
የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ..... 9
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ..... 9
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA) ..... 9
የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የስራ ሂደት መግለጫ /PROCESS DESCRIPTION/ ..... 10
ክፍል ሁለት ..... 11
የኦዲት ግኝቶች ..... 11
2.1 ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን በቁርኝት ፕሮግራም አቅሙን በመገንባት የሚያደርገውን የድጋፍ እና የክትትል ሥራዎች አፈፃፀም በተመለከተ፤ ..... 11
የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፤ ..... 11
የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ፡ ..... 12
የቁርኝት ፕሮግራም ግብአትን በመጠቀም የዘርፉን አምራቾች ክፍተት በመለየት እቅድ አዘጋጅቶ ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤ ..... 14

ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ........ 17

በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ስላለው ግንኙነትና ትስስር በተመለከተ፡- ........ 19

በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት የጥናትና ምርምር ስራዎች ስለመካሄዳቸው፣ ውጤቱንም ስለመታተሙ እና ሲምፖዚየም ሰለመዘጋጀቱ፣ ........ 23

በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት በማካሄድ ድጋፍና የምክር አገልግሎት ስለመሰጠቱ፣ ........ 25

የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 26

በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ላለው የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና ስለመስጠቱ እና ድጋፍና ክትትል ስለማድረጉ፣ ........ 28

በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች የተዘጋጁ፣ ሥርዓተ-ትምህርቶች የተቀረጹ፣ ለአጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ማንዋሎች እና ሞጁላር ኮርሶች ስለመዘጋጀታቸው፣ ........ 31

ኢንስቲትዩቱ በቁርኝት ስምምነቱ መሰረት ለዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ ክትትል ስለማድረጉና ስለማመቻቸቱ፣ ........ 32

በቁርኝት ፕሮግራሙ ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎች እና ዘዴዎችን መነደፋቸውን በተመለከተ፤ ........ 33

ኢንስቲትዩቱ የኢንስቲትዩቱ እና የዘርፉ ኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ማመቻቸቱን በተመለከተ፤ ........ 35

ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር መሰረት ስለመፈጸሙ መከታተሉን እና መገምገሙን በተመለከተ፣ ........ 36

ክፍል ሦስት ........ 44

የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 44

ክፍል አራት ........ 47

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 47

አባሪ 2፡ የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር ........ 55

አባሪ 3፡ የኢኒስቲትዩቱ የሚሰጣቸው ድጋፍና አገልግሎቶች ........ 56

በኢንስቲትዩቱ የጨርቃጨርቅ ልማት ዘርፍ ሥር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡዋቸው ድጋፍና አገልግሎቶች ........ 56

በኢንስቲትዩቱ የቴክኒክ ዘርፍ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡአቸው ድጋፍና አገልግሎቶች ........ 58

በኢንስቲትዩቱ የጥጥ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡአቸው ድጋፍና አገልግሎቶች ........ 60

አባሪ 5 ........ 63

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive Summery)

የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኝት ፕሮግራም፣ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኝት ፕሮግራም፣ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2007 እስከ 2010 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦችን አስቀምጠናል፡፡

- የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ አስቀድሞ ፕሮግራሙ በኢንስቲትዩቱ ለማካሄድ የሚረዳ የተጠና የዳሰሳም ሆነ ሌላ አይነት ጥናት የሌለ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) እና ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ጋር በተፈራረመው ስምምነት መሰረት በፕሮግራሙ ትግበራ የዘርፉን ኢንዱስትሪዎችን ማካተት እንደሚገባ ቢገልጽም እንዲካተቱ አለመደረጋቸው፡፣
- የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር በዘርፉ አምራቾች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የተያዘ እቅድ እና ሽግግሩን ተግባራዊ የሚደረግባቸው አምራቾች የሚመረጡበት መስፈርት የሌለ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ያላዘጋጀ መሆኑ፣

- የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ ስራ እና  የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ የሚደረገው ድጋፍ ውስንነት ያለበት መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የኢንስቲትቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር እንዲጠናቀቅ የሚያደርገው ክትትል እና ግምገማ ከሚያዘው የግምገማ መርሃ ግብር ውጭ መሆኑና የግምገማ ኮሚቴው ኢንዱስትሪዎችን ማሳተፍ የነበረበት ቢሆንም ያላሳተፈ እንዲሁም የፕሮግራሙ ትግበራ በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ረገድ ያመጣውን ውጤት የማይገመግም መሆኑ፤
- ፕሮግራሙ በተያዘለት የጊዜ ገደብ NIFT ሰኔ 2010 ዓ.ም ፣ ICT ጥር 2010 ዓ.ም እና IIT ሀምሌ 2010 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን ከአጠቃላይ ከተመደበው በጀት ስራ ላይ የዋለው ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ 62.3 ከመቶ በመሆኑ ከጊዜ ገደብ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ፡፡

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ኢኒስቲትዩቱ ለወደፊቱ የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ አስቀድሞ ፕሮግራሙ ከመከናወኑ በፊት በዘርፉም ሆነ በኢኒስቲጥዩቱ በቁርኝት ፕሮግራም መሞላት ያለበት ክፍተትና ችግር መኖሩን የሚሳይ ጥናት ሊያከናውን እንዲሁም ፕሮግራሙ በአገር ውስጥ ባለ አቅም ሊሸፈን አለመቻሉ ሊያረጋገጥ እንደሚገባ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) እና ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ጋር በተፈራረመው ስምምነት መሰረት በፕሮግራሙ ትግበራ የዘርፉን ኢንዱስትሪዎችን ማካተት እንደሚገባው፤
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት ፕሮግራም የሚገኘውን እውቀት ወደ ፋብሪካዎች በሚፈለገው ደረጃ ለማሸጋገር እና እንደየክፍተታቸውና የሙያ መስክ

አንፃር ድጋፍ እንዲያገኙ የእውቀት ሽግግር ንድፈ ሀሳብ ወይም እቅድ ማዘጋጀት እንዳለበት፣

- ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ማዘጋጀት እንዳለበት፤
- የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ ስራ እና የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ የሚደረገው ድጋፍ ማጠናከር እንዳለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ የኢንስቲትቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ማድረግ እንዳለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር እንዲጠናቀቅ የሚያደርገው ክትትል እና ግምገማ በተያዘው የግምገማ መርሃ ግብር መደረግ እና የፕሮግራሙ ትግበራ በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ረገድ ያመጣውን ውጤት መገምገም እንዳለበት፤

የማሻሻያ ሃሳብ ሰጥተናል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓት የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ በነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጎላ ሚና መጫወት ከሚጠበቅባቸው አግሮ ኢንዱስትሪዎች መካከል ጥጥ እና የጨርቃጨርቅ ልማት ተጠቃሽ እና ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የጥጥ ምርት እና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች በመሰረቱ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ በግብርና ከሚመራው ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር በሚደረገው ሽግግር የላቀ ሚና የሚጫወተው የማኑፋክቸሪንግ እንዱስትሪ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ዘርፉን መሪ አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡
2. ይህንን ዘርፍ የትኩረት ማዕከሉ አድርጎ ለመደገፍ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ እንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዘርፉን በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችሉ ተልእኮዎችን መተግበር ከጀመረ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ የራሱን አቅም በሂደት እየገነባ ቀላል የማይባሉ የዘርፉ እድገት ማነቆዎችን በመፍታት በሀገሪቱ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ እየታዩ ያሉትን ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እንደ ዋና ግብዓት ሆነው ኢንቨስትመንት የማስፋፋት፣ የማማከር፣ የምርምርና ስርፀት፣ የስልጠና፣ የቤንች ማርኪንግ፣ የላብራቶሪ እና የግብይት ድጋፍና አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ሌሎች ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

## የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አመሰራረት

3. በጨርቃጨርቅና ስፌት ዘርፍ ለተሰማሩ እና ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶች ድጋፍ እና አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002 ተቋቁሞ ዘርፉን ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ በመቀጠልም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ለማሻሻል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 286/2013 መሰረት የጥጥ ልማቱንና ግብይቱን ከጨርቃጨርቅ እና ስፌት ዘርፉ ጋር ጨምሮ ድጋፍ እና አገልግሎቱን

እንዲሰጥ የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በአዲስ መልክ ተቋቁሟል፡፡ በዚህ መሰረት የፋብሪካዎችን የተወዳዳሪነት አቅምና የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ የኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የአቅም ግንባታ፣ የምርት ግብዓት ትስስርና የገበያ ድርሻን ማስፋፋት የሚያስችሉ ድጋፍ እና አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል፡፡

4. ኢንስቲቱዩቱ ብቃት ያለው ድጋፍ እና አገልግሎት ለመስጠት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት እንዲችል በጋርመንት ቴክኖሎጂ፣ በጥጥ እና ጨርቃጨርቅ ግብይት የሥራ መስኮች

- ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ከመጋቢት 2005 ዓ/ም ጀምሮ፣
- በማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ከሀምሌ 2006 ዓ/ም ጀምሮ እና
- በጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ፣ በሽመናና ሹራብ ቴክኖሎጂ፣ በምርምር እና ላብራቶሪ እና የኢንጂነሪንግ፣ ኢነርጂና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የስራ መስኮች ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) ከጥር 2007 ዓ/ም ጀምሮ

ከተቋማቱ ጋር ለሶስት አመታት በተደረገው የቁርኝት ስምምነት በከፍተኛ ትምህርት፣ በአጫጭር ስልጠናዎች፣ በሥራ ላይ ስልጠና እና የልምድ ልውውጥ የኢንስቲቱዩቱን አቅም ከመገንባት በተጨማሪ ለጨርቃጨርቅ እና ስፌት ፋብሪካዎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ፕሮግራም መጋቢት 2005 ዓ/ም ተጀምሮ እንደገና ሰኔ 2007 ዓ/ም ማሻሻያ ተደርጎለት ሰኔ 2010 ዓ/ም ይጠናቀቃል፣ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ፕሮግራም ሀምሌ 2006 ዓ/ም ተጀምሮ ጥር 2010 ዓ/ም ይጠናቀቃል፣ ኢንዲያን ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) ጥር 2007 ዓ/ም ተጀምሮ ሀምሌ 2010 ዓ/ም ይጠናቀቃል፡፡

5. በዚሁ መሰረት በቁርኝት ፕሮጀክቶች ለሶስት ተከታታይ አመታት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማካሄድ ብቃት ያለው ተቋም ለማድረግ በቁርኝት ፕሮጀክት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

  - የኢንስቲቱዩትን የአሰራር ሥርዓቶች ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣

- ➢ ለዘርፉ ፋብሪካዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣ ፋብሪካዎችን ኦዲት ማድረግና ያሉትን ክፍተቶች በመዳሰስ የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብና መደገፍ፤
- ➢ በኢንስቲትዩቱ፣ በፋብሪካዎች እና በከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን የሶስትዮሽ ትስስር መፍጠርና ተግባራዊ ማድረግ፤
- ➢ የኢንስቲትዩቱ የኬሚካልና የአካባቢ ላቡራቶሪዎች እውቅና እንዲያገኙ ማስቻል፡፡
- ➢ በፋብሪካዎች ደረጃ የምርጥ ተሞክሮ ትግበራ ማካሄድ፤
- ➢ ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችና አመራሮች አጭር ስልጠና እና የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት በህንድ ሀገር ማመቻቸት፣

እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ራዕይ፣ ተልኮ እና ዓላማ

**ራዕይ**

6. የኢትዮጵያን የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ከአፍሪካ ቀዳሚ በማድረግ በ2017 በአለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ታዋቂ ከሆኑ አገሮች ተርታ ማሰለፍ፡፡

**ተልዕኮ**

7. የኢትዮጵያን የጥጥ ልማት እና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት፤ የማማከር፤ የምርምርና ሥርፀት፤ የሰው ኃይል ልማት፤ የደረጃ ዝግጅት ፤የጥራት ፍተሻ፤ የግብዓት አቅርቦት እና የግብይት ድጋፍ እና አገልግሎት በመስጠት የዘርፉን ልማት ማፋጠን፤

**አላማ**

8. የጥጥ ልማትን እና የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂዎች ልማትና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት፤

## የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

9. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል በወጣው የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 286/2005 ዓ/ም መሠረት ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰቶታል: -

- ❖ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችንና መርሃግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
- ❖ ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
- ❖ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈጻጸም ችግሮች ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤
- ❖ በጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት ዘርፍ ለሚሰሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
- ❖ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራ አመራርና፣ ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፣ ለሰልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፤
- ❖ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤
- ❖ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
- ❖ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

- የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፤
- ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤
- የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፤
- ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፤
- ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ስራ ማከናወን፤
- ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፤
- የመንግስትን አገራዊ የጥጥ ልማት ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ማናቸውንም፣ ከጥጥ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማስተባበር፣ መቆጣጠርና ማስፈጸም፤
- ከሚመለከታቸው አካት ጋር በመተባበር በጥጥ ልማት ለመሰማራት ለሚያመለክቱ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦትን፣ ማስተላለፍንና ማስተዳደርን በሚመለከት ድጋፍ ማድረግ፤
- ለጥጥ ልማትና ግብይት ፖሊሲ ቀረጻ የሚያግዙ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ሲፀድቁም የአፈጻጸም ማኑዋሎችን ማዘጋጀትና እንዲተገበሩ ማድረግ፣ የዘርፉን ቀጣይ እድገት የሚያረጋግጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- ለጥጥ ልማቱ ድጋፍ የሚያደርጉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ማስተባበር እና በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ፤
- ሰፋፊ እና ሜካናይዝድ የጥጥ እርሻዎች ሊለሙባቸው የሚችሉ አካባቢዎችን መለየትና የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ድጋፍ ማድረግ፣ ሜካናይዝድ የጥጥ እርሻዎችን የሚያለሙ ባለሀብቶች ያላቸውን ይዞታ ለማስፋፋትም ሆነ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንዲችሉ ከሚመለከታቸው ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- ለዘርፉ ድጋፍ የሚያደርጉ የምርምር ተቋማትን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ የጥጥና የጨርቃጨርቅ አምራች ማህበራትን፣ እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ

ድርጅቶችን በማቀናጀት በዘርፉ ችግሮች ላይ ምርምሮች ማካሄድና የምርምር ዉጤቶቹ ሲፀድቁ ተግባራዊ ማድረግ፣

- በጥጥ ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶች የምርት ጥራትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችሉ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚያገኙበትን እና ከአርሶ አደሩ ጋር በማስተሳሰር ህብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣
- የጥጥ ልማት ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ ከሚመለከታቸው አካት ጋር ተባብሮ መስራት፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብይት መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ የገበያ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የገበያ ማዕከላቱን አቅም መገንባት እና ግብይቱ የጥጥ ጥራትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲከናወን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- በጥጥ ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶችን የሥራ እንቅስቃሴ መከታተልና የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ድጋፍ ማድረግ፣
- የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችን የገበያ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ጥራቱን የጠበቀ ጥጥ ለማምረት የሚያግዝ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲደረግ መደገፍ፣
- በጥጥ ልማቱና ግብይቱ ላይ የነበሩና ያልተፈቱ ችግሮችን መለየትና ችግር ፈቺ አሰራሮችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ መደገፍ፣
- የጥጥ ልማቱንና ግብይቱን በተሻለ መንገድ ለመምራትና ለመደገፍ የሚያስችል እቅድ መንደፍ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ ሪፖርት ማቅረብ እና በጥጥ ልማትና ግብይት ላይ መንግስትን ማማከር፣
- ለጥጥ ምርት በሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ በአመራረት ሂደቱ እና ምርቱን በማጓጓዝና በማከማቸት ረገድ የጥራት ቁጥጥርና የምክር አገልግሎቶችን መስጠት፣
- በጥጥ ልማት አካባቢዎች መለስተኛ ላብራቶሪዎችን ማደራጀትና የጥጥ ምርት ጥራት ፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣
- ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፣
- ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፣
- የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን፡፡

## የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

10. ኢንስቲትዩቱ የሚመራው በዋና ዳይሬክተር ሲሆን በዋና ዳይሬክተር ስር የእቅድ እና መረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳሬክቶሬት፣ የፋይናንስና ሎጂስቲክስ ስራ አመራር፣ የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት፣ የኦዲት አገልግሎት፤ በጨርቃጨርቅ ልማት ዘርፍ፡- የጥጥ መዳመጫ እና የፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የሽመናና ሹራብ ስራዎች ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ ማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፤ በቴክኒክ ዘርፍ፡- የኢንጂነሪንግ፣ የኢንፎርሜሽንና ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የጥጥ እና የጨርቃጨርቅ ግብይት ዳይሬክቶሬት፣ ምርምር ላብራቶሪ ዳይሬክቶሬት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት፤ እንዲሁም የጥጥልማት ዘርፍ፡- የጥጥ ልማት ዳይሬክቶሬት እና የጥጥ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በመሆን ተዋቅሯል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. በኢንስቲትዩቱ 636 የሰው ኃይል እንዲኖሩት በመዋቅር የተፈቀደለት ሲሆን በታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም ወንድ 192 እና ሴት 107 በድምሩ 299 ሰራተኞች አሉት፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ማስተርስ ዲግሪ 46 ፣ ዲግሪ 145፣ ዲፕሎማ 53 እና ከ 8ተኛ-12ተኛ ክፍል 57 በጠቅላላው 299 ሠራተኞች በኢንስቲትዩቱ ይገኛሉ፡፡

## የኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ

12. የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት ግምጃ ቤት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ከመንግስት ግምጃ ቤት የቁርኝት ፕሮግራምን ጨምሮ የተመደበና ስራ ላይ የዋለ በጀት (በኢትዮጵያ ብር)**

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት በብር | ስራ ላይ የዋለ በጀት በብር | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 153,488,870 | 56,785,873.4 | 39 % |
| 2008 | 159,314,340 | 71,393,390.67 | 45 % |
| 2009 | 193,280,490 | 100,555,553.91 | 52 % |

**ለቁርኝት ፕሮግራም ብቻ የተፈቀደና ስራ ላይ የዋለ ገንዘብ (በአሜሪካን ዶላር)**

| ፕሮግራም | አጠቃላይ የተፈቀደ በጀት በአሜሪካን ዶላር | አጠቃላይ ስራ ላይ የዋለ በጀት በአሜሪካን ዶላር | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ % |
|---|---|---|---|
| NIFT | 4,263,440.08 | 3,079,712.87 | 72.2% |
| ICT | 1,998,665.00 | 1,131,127.60 | 56.6% |
| IIT | 1,059,870.00 | 349,246.02 | 33% |
| ድምር | 7,321,975.08 | 4,560,086.49 | 62.3% |

## የኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኝት ፕሮግራም፣ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

14. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2007 እስከ 2010 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

15. ኦዲቱ በዋናነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆን ዋና ባለድሻ አካላት ከሆኑት የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዘጠኝ ኢንዱስትሪዎች፣ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሁለት የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት

በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከቁርኝት ፕሮግራም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ጠይቆ በመከለስ ነው፡፡ በናሙና የታዩት ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) "የቁርኝት ፕሮግራም፤ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

17. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) አንድ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) ተዘጋጅቷል፡፡ እሱም፡-

   I. ኢንስቲቱዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን **በቁርኝት ፕሮግራም አቅሙን በመገንባት** በሰው ሀይል ልማት፣ በማማከር፤ በምርምርና ስርፀት፤በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ በጥራት ፍተሻ፣ በቴክኒክና እና በግብይት **ለኢንዱስትሪዎች የሚያደርገው የድጋፍ እና የክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ** ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ የሚል ነው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

18. ከላይ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 34 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ኢንስቲትዩቱ ከሀምሌ 2005 ዓ/ም ጀምሮ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT)፣ ከሀምሌ 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) እንዲሁም ከሀምሌ 2007 ዓ/ም ጀምሮ ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) ጋር ለሶስት አመታት የተደረጉት የቁርኝት ስምምነቶች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ለኢንስቲትዩቱ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ **የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡**

19. በኢንስቲትዩቱ የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የሽመናና ሹራብ ሥራ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የምርምር ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት፣ የኢንጅነሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ኢነርጂ ዳይሬክቶሬት፣ የጥጥ እና ጨርቃጨርቅ ግብይት ዳይሬክቶሬት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስልጠና ዳይሬክቶሬት፣ የጥጥ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት እና የጥጥ ልማት ዳይሬክቶሬት የሥራ ክፍሎችን ያለውን የሥራ ሂደት ፍሰት **በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡**

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን በቁርኝት ፕሮግራም አቅሙን በመገንባት የሚያደርገውን የድጋፍ እና የክትትል ሥራዎች አፈፃፀም በተመለከተ፤

### የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፤

20. የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት ጥናት ሊከናወንና በተጠናው ጥናት መሰረት ፕሮግራሙ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት በቅድሚያ ስለቁርኝት ፕሮግራሙ አስፈላጊነት እና እንዴት መተግበር እንዳለበት በኢንስቲትዩቱም ሆነ በሌላ አካል የተጠና ጥናት ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

22. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት አስተያየት የቁርኝት ፕሮግራም ከመከናወኑ በፊት የአቅም ክፍተት መኖሩን ያረጋገጠና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ሊኖሩ እንደሚገቡ/ አስፈላጊነት ላይ የተካሄደ የጥናት ሰነድ/ ቢዝነስ ፕላን እንዳለ፣ የቁርኝት ፕሮግራም የተደረገው የኢንስቲትዩቱን አቅም ለማጎልበት ተብሎ ከመሰል ተቋም/ኢንስቲትዩት ጋር ነው፡፡ በተከናወነው ጥናት /በቢዝነስ ፕላኑ የተመለከተው የቁርኝት በሚል ቃል በቃል ሳይሆን ኢንስቲትዩቱ ሥራ ሲጀምር የአቅም ውስንነት ያለው በመሆኑ የሰው ኃይሉን እና ኢንዱስትሪውን አቅም የሚያጎለብቱ የውጭ ሙያተኞች መቅጠር እንደሚገባ በሚል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

23. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ሊኖሩ እንደሚገቡ/ አስፈላጊነታቸው ላይ የተካሄደ የጥናት ሰነድ/ ቢዝነስ ፕላን መኖሩን የቁርኝት ፕሮግራም በብሔራዊ ደረጃ እውቅና አግኝቶ ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ኢንዱስትሪ ለመደገፍ የተሰጠውን ሰፊ ተልዕኮ ለማከናወን የሚያስችል የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት እንዳለበት ታምኖበት መንግስት ከህንድ መንግስት ጋር በተደረሰ መግባባት ይህ ክፍተት ለመሙላት የተቀረፀ የኢንስቲትዩቱ የአቅም መገንቢያ

ፕሮግራም መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና እንዲሁም ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

24. ይሁን እንጂ የተጠናው ጥናት ኢንስቲትዩቱ ያለውን የአቅም ክፍተት ለመሙላት የቁርኝት ፕሮግራም እንደሚያስፈልግና መቼ መፈጸም እንደሚገባው የሚያሳይ ባለመሆኑ እንዲሁም ለረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ተያይዞ የቀረበው የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ (MoU) ጥናቱን ሊወክል ስለማይችል አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

25. የቁርኝት ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት ስለቁርኝት ፕሮግራም አስፈላጊነትና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የአቅም ክፍተት በጥናት ላይ ተመስርቶ ካልተለየ፣ የፕሮግራሙ አላማና ግብ በግልጽ ካልተተገበረ ያገኘውን ፋይዳ ለመገምገምና ለመለካት፣ ስምምነቱም የዘርፉን/የኢንስቲትዩቱን አቅም የሚገነባ ፕሮግራም መሆኑን ማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ፡**

26. የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበት የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በሚመለከተው አካል ሊፀድቅ እንዲሁም አምራቾች በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ሊመረጡ ይገባል፡፡

27. ኢኒስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) እና ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ጋር በገባው የቁርኝት ፕሮግራም ላይ በዘርፉ የተሰማሩ ኢንሰዱስትሪዎች እንደሚሳተፉ በስምምነት ሰነዱ ላይ ተካቷል ፡፡ ለማሳያ ያህል

ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT)

- The scope of responsibilities of the twinning partner shall be capacity building of TIDI and providing services to the industry which includes the following activities (NIFT, page 6 of 11): Provide training on maintenance of machineries for TIDI staff and to the industry ( NIFT, page 7 of 11,# 5)፣ Provide technical support in all the spheres of garment sector (NIFT, page 7 of 11,# 8)፣ Provide services to the industry such as testing, certification and

establishing norms and standards (NIFT, page 7 of 11, #9)፣ Follow up and audit the performance of the companies and propose/take corrective actions (NIFT, page 7 of 11,# 15)፣

ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT)

The specific objectives of the proposed project ( the ICT and ETIDI tiwinning program) are ( ICT, page 5 of 21, # 5.3)፣ Provide services to the industry such as testing, certification and establishing norms and standards (ICT, page 5 of 21)፣ Support the industry in developing its human resources at managerial, technical and skilled work force levels by providing specialized training (ICT, page 5 of 21)፣Impliment benchimarking at company level and also monitor bench marking implimentetion by other consulting firms in collaboration with the industry (ICT, page 5 of 21)፣ ይገኙበታል፡፡ (ቀሪዎቹ በአባሪ 4 ላይ ተያይዘዋል፡፡)

28. ይሁን እንጅ በኢኒስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸውን አምራቾች ለመምረጥ የሚያስችል የተዘጋጀ መስፈርት አለመኖሩን እና በኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ግብአት ሽግግር ተብለው የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች የሌሉ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

29. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት እና በመውጫ ስብሰባ እንዲሁም በመመዘኛ መስፈርት ላይ አስተያየት በሰጡበት ወቅት የቁርኝት ፕሮግራም አላማ ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ሳይሆን የኢንስቲትዩቱን አቅም ለማጎልበት መሆኑን እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ወደ ፋብሪካው የሚሄዱት በቁርኝት አማካኝነት ኢንዱስትሪዎች ላይ የስራ ላይ ልምምድ ለማድረግ መሆኑን እና ኢንዱስትሪዎች ለልምምድ ተግባር የሚመረጡት ከኢንዱስትሪው የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ እና ከኤክስፖርት አፈጻጸማቸው አንፃር መሆኑንና በአጠቃላይ ኢንዱስትሪዎች የሚመረጡት ከቁርኝት ፕሮግራም እነሱን ተጠቃሚ ለማድረግ ሳይሆን የኢንስቲትዩቱን ባለሙያዎች ለማሰልጠን በሚል እንደሆነና ኢንዱስትሪዎችንም የሚደግፉት በመደበኛ የድጋፍና ክትትል ሥራ እንደ ኢንስቲትዩቱ እቅድ እና ፕሮግራም እንጂ ቁርኝት ብቻ ተነጥሎ የማይተገበር መሆኑን እና በተለየ አግባብ ለቁርኝት ፕሮግራም ተብሎ ሊመረጡ የሚገቡ

አምራቾች/ ፋብሪካዎች የሌሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የቁርኝቱ አላማ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች የዘርፉ ኢንዱስትሪ ለመደገፍ የሚያስችላቸውን እውቀት ማስተላለፍ የሚል እና ከውል ስምምነት ሰነድ ላይ ያለ ሳይሆን ከውል ስምምነት ሰነዱ ጋር አባሪ በተደረገው የፍላጎት መግለጫ ቢጋር (TOR) በዘርፉ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች በቅድሚያ ከቁርኝት አጋሮች ቀጥታ ከፕሮግራሙ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የተቀመጠ አይደለም በማለት ለረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

30. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም የፍላጎት መግለጫ ቢጋሩ (TOR) የተፈረመው ውል አካ እና ቁርኝት አጋሩ እንዲፈጸም የሚጠበቁ ነገሮችን የሚዘረዝር በመሆኑ እና ለመተግበር የቁርኝት አጋሮች መስማማታቸውን በመፈራረማቸው እና ለልምምድ የሚካድባቸው ፋብሪካዎች መምረጫ ግልጽ መስፈርት መውጣት ስለነበረበት የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

31. ከቁርኝት ፕሮግራም የተገኘውን የቴክኖሎጂ እውቀት ለኢንዱስትሪዎች በስምምነቱ መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አለመደረጉ የእውቀት ሽግግሩ በፕሮግራም እና በእቅድ እንዳይከናወን ከማድረጉም በላይ ኢንዱስትሪዎች ባላቸው ክፍተትና የሙያ መስክ ተገቢውን ስልጠና እና ድጋፍ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

**የቁርኝት ፕሮግራም ግብአትን በመጠቀም የዘርፉን አምራቾች ክፍተት በመለየት እቅድ አዘጋጅቶ ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤**

32. ኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ፕሮግራም ግብአት ሽግግር እቅድ በመያዝ የአምራቾችን ክፍተት በመለየት በክፍተቱ መሰረት ሊደግፍ፤ የማረጋገጫ ዝርዝር አዘጋጅቶ ሊከታተልና ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

33. ኢንስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT, activities on page 7 of 11 and and 9 of 26) እና ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT, activities on page 5 of 21) የቁርኝት ስምምነት ሰነድ ላይ የአምራቾቹን ክፍተት በመለየት ድጋፍ መስጠት እንዳለባቸው ተቀምጧል፡፡ ለማሳም ያህል

ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT)

- The scope of responsibilities of the twinning partner shall be capacity building of TIDI and providing services to the industry which includes the following activities (NIFT, page 6 of 11):
    - Follow up and audit the performance of the companies and propose/take corrective actions (NIFT, page 7 of 11, # 15) ፣
    - Identify key areas of intervention for making the garment sector globally competitive in terms of fulfilling compliance requirements (NIFT, page 7 of 11, # 12)

ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT)

- The specific objectives of the proposed project (the ICT and ETIDI tiwinning program) are (ICT, page 5 of 21, # 5.3)
    - Identify key areas of intervention for making the Textile Processing sctor globally competitive in terms of fulfilling compliance requirements (ICT, page 5 of 21)
    - Develop support packages, wich will streangthen strategically the competitive advantage of the Ethiopian Textile Processing sctor (ICT, page 5 of 21)
    - Support the industry in developing its human resources at managerial, technical and skilled work force levels by providing specialized training (ICT, page 5 of 21)
    - Impliment benchimarking at company level and also monitor bench marking implimentetion by other consulting firms in collaboration with the industry (ICT, page 5 of 21)

የሚሉት ይገኙበታል፡፡ (ቀሪዎቹ በአባሪ 5 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡)

34. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በማኔጅመንትና በቁርኝት የተማሩ ባለሙያዎች ጋር በ 18/07/09 እና መጋቢት 2009 በተደረገው የማኔጅመንት ስብሰባ ላይ ኢንስቲትዩቱ ለፋብሪካዎች የሚያደርገው ድጋፍ፣ ግብረ መልስ መስጠት ላይ፣ ዕቅድ ክንውን በትክክል አዘጋጅቶ መላክ ላይ፤ የክትትል ስልቱ ተከታታይነት መኖሩ ላይ ክፍተት መኖሩን፤ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ መስራት

የሚገባውን ያልሰራ መሆኑን፣ በተለይ ከግብይት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ፋብሪካዎች ላይ ያለውን ችግር ለይቶ ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ ላይ የትኩረት ማነስ መኖሩን እና ምርትና ምርታማነትን ለመደገፍ ክፍተት ያልተለየ መሆኑን እንዲሁም ከቁርኝት ፕሮግራም የተገኘውን አቅም ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ለኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠው መልስ የቁርኝት ፕሮግራም አሳታፊ አለመሆኑን፣ ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራምን ከሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎች፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች የአሰራር ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀሙ ያሉ ፋብሪካዎችን በመውሰድ የልምድ ልውውጥ እንዲኖር የማድረግ ተግባር ላይ መስመሩ ዝግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- ለባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ ምክትል ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ክፍተት ተለይቶ (Gap analysis) በኢንስቲትዩቱ ተሰርቶ በላብራቶሪ መሳሪያ ቴክኒካል ድጋፍ የተሰጠ ቢሆንም ክትትል የማድረጉ ሁኔታ ክፍተት ያለበት መሆኑን፣ የፋብሪካው አፈጻጸም ካለፉት ሁለት አመታት ጀምሮ ሲዳከም ወይም ኪሳራ ሲያጋጥመው ፋብሪካው ያጋጠመውን ችግር እንደ ኢንስቲትዩት የጠየቀበት፣ የተከታተለበት እና የደገፈበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

35. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና በመውጫ ስብሰባ የሰጡት አስተያየት ስልጠና በመስጠት ረገድ ኢንዱስትሪዎችን በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ እየተደረገ መሆኑ መግለጻቸው እና የቁርኝት አላማ ለፋብሪካው ቀጥታ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ አለመሆኑና ቁርኝት የሚለካው ኢንስቲትዩት ውስጥ በሚፈጠረው የባለሙያ አቅም እንጂ በኢንዱስትሪ ተደራሽነትን እንደማይለካ እና የዘርፉ ፋብሪካዎች የተለያዩ መድረኮችን እና ወርክሾፕ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ እና የእውቀት ሽግግር የሚደረግበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም የቁርኝት ፕሮግራም ብቻ ተለይቶ የአምራቾችን ክፍተት በመለየት ድጋፍ ለማድረግ የተዘጋጀ እቅድ እና ዘዴ የሌለ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ የቁርኝት ፕሮግራሙ በመደበኛ ስራ ውስጥ በማካተት የሚሰራና የኢንስቲትዩቱን አቅም በማጎልበት የመደበኛ ስራን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚተገበር ፕሮግራም እንጂ የቁርኝት ፕሮግራም ከተቋሙ የመፈፀምና የማስፈፀም

አቅም ግንባታ ውጭ ሊተገበር እንደማይገባ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የቁርኝት ፕሮግራም በኢንስቲትዩቱ መደበኛ ስራዎች (የኢንዱስትሪ የቴክኒክ ድጋፍ፤ የምርጥ ተሞክሮ ትግበራ እና በስራ ላይ ስልጠና) በማካተት ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡ በመደበኛ ስራቸው እቅድ መሰረት ድጋፍ ማድረጋቸው ገልፀዋል ለምሳሌ ባህርዳር፤ ኮመቦልቻ፤ ኤልቴክስ፤ አልመዳና ማ ጋርመንት የክፍተት መለይት ስራ እና የቴክኒካል ድጋፍ ማድረጋቸውን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ እንዲሁም ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

36. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም በውል ስምምነቶቹ ላይ የዘርፉ ፋብሪካዎችን መደገፍ፣ ማብቃት፣ ኦዲት ማድረግ እና መከታተል እንደሚገባ በግልጽ በመቀመጡ እንዲሁም ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት ለኦዲት ግኝት ተራ ቁጥር 33 መደገፍያ ማሰረጃ መግለጫ ላይ standard operating procedure OE Spinning, standard operating procedure daily air cleaning እና Capacity building through bench marking (ባህርዳር ጨርቃጨርቅ) የተገለፀው ከቁርኝት አጋር ስምምነት ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው Texcoms Textiles Solutions (TTS) በተባለ ድርጅት የተተገበረ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

37. ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም ግብአት ሽግግር ለመተግበር ንድፈ ሀሳብ ወይም እቅድ ባለማዘጋጀቱ ከቁርኝት ፕሮግራም የሚገኘውን እውቀት ወደ ፋብሪካዎች ለማሸጋገር አመች ሁኔታ እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ ከቁርኝት ፕሮግራም የሚገኘው የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ግብአት በሚፈለገው መጠን ወደ ፋብሪካዎች እንዳይደርስ ያደርገዋል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

38. ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃ ግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፤

39. ኢኒስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) Responsibilities of client;

- it shall facilitate consultation meeting between the identified beneficiary Apparel manufacturing companies and the experts from Twinning Partner to prepare mutually agreeable beneficiary oriented Action Plan and norms for performance evaluation (NIFT, page 19 of 26) እንዲከናውን የቁርኝት ስምምነት ተገብቷል፡፡

40. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው የታዩት ፋብሪካዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቁርኝት ፕሮግራም ለፋብሪካው የሚያደርገው እና ማድረግ የሚገባው ምን እንደሆነ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በምን መልኩ ወደፋብሪካው ወርዶ የቁርኝት ፕሮግራምን እንደሚተገብር የማያውቁ መሆኑን እና በኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃ ግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የምክክር መድረክ የሌለ መሆኑን፣ ኢንዱስትሪዎችን፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማቶችን እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ያማከለ ሴሚናር ተዘጋጅቶ የተለያዩ ጥናቶች የቀረቡበት እና የእውቀት ሽግግር የተደረገበት መድረክ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠው አስተያየት የቁርኝት ስምምነት የኢንስቲትዩቱን አቅም ለመገንባት በሁለቱም ተቋማት የሚፈጸም እንደሆነና አፈጻጸሙም በውል ስምምነቱ ውስጥ የሚጠበቁ ውጤቶች እና ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት እንደሚገመገም ገልጸዋል፡፡

42. የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም በስምምነት ሰነዶች ላይ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃ ግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ማዘጋጀት ስለነበረበት የተሰጠውን ምላሽ እንዳለ ለመቀበል ያቸግራል፡፡

43. በኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የጋራ የምክክር መድረክ መዘጋጀት እንዳለበት በስምምነት ሰነዱ ላይ የተቀመጠ በመሆኑና ይህ ባለመደረጉ ፋብሪካዎች በፕሮግራሙ ሊኖራቸው የሚገባው ድርሻ ካለመለየቱም ባሻገር ኃላፊነታቸውን

እንዳይወጡ እና ከቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ ማግኘት የሚገባቸውን እውቀት እና ልምድ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

## በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ስላለው ግንኙነትና ትስስር በተመለከተ፡-

44. ኢንስቲትዩቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት (በዘርፉ የሰው ኃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ) ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር ሊያሳድግ ይገባል፡፡ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ሊሰራና በጋራ የምርምር ሥራዎችን ሊያካሂድ፤ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ሊያሰለጥን፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ ሊሰራና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት (በዘርፉ የሰው ኃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ) ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር ማሳደግ እንደሚገባ የቁርኝት አጋር ስምምነት ሰነድ ላይ
Introduce and Implement tripartite linkage system among the Industry, ETIDI, higher institutions and TVET for human resource development, research, technology transfer etc. (ICT page 6 of 21) and to design and put in place systems for promoting, interactions and linkages with the industry, TIDI, TVETs and/or institutions of higher learning for human resource development, research, and technology transfer (NIFT, page 9 of 26, ii) በማለት የተገለፀ ቢሆንም የተባለውን ግንኙነትና ትስስርን የማሳደግ ሥራ ክፍተቶች እንዳሉበት ታውቋል፡፡

46. በናሙና ተመርጠው የታዩት ፋብሪካዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣

- በኢንስቲትዩቱ አማካኝነት የተዘጋጀ በተቋማቱ መካከል የተደረገ የሶስትዮሽ ትስስር የሌለ መሆኑን፤ እንዲሁም ተቋማቱ በራሳቸው በሚያደርጉት ትስስር ላይም እንኳን ትስስራቸው እንዲያድግ ኢንስቲትዩቱ ያደረገላቸው ድጋፍ እና

ክትትል የሌለ መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩት ፋብሪካዎች መግለጻቸው፣

- ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ለባህርዳር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፤ ለኮምቦልቻ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለቀረበላችው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በኢንስቲትዩቱ የተመሰረተ ኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ፎረም ያለ ቢሆንም ፎረሙን ከመመስረት የዘለለ የተሰራ ስራ እንደሌለና ትስስሩ እንዲያድግ የማድረግ ስራ እና ድጋፍ ክፍተት ያለበት መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

47. እንዲሁም በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የEthiopian Institute of textile & fashion technology (EITEX) የስራ ሃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርሲቲው የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ለኢንስቲትዩቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በማሰልጠን ይደግፋል፡፡ ኢኒስቲትዩቱ ለዩኒቨርሲቲው የድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርብ እንደ አስፈላጊነቱ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ እንደሚያደርግ እና ለሰባት ባለሙያዎችም ስልጠና እንደሰጠ፣ በሌላ በኩልም በባህርዳር ዩኒቨርሲቲና በኢንስቲትዩቱ የጋራ ስምምነት ሰነዶች (MOU) ላይ ጥናትና ምርምር በጋራ እንደሚሰሩ ቢቀመጥም እስካሁን ዩኒቨርሲቲው በግሉ እየሰራ እንደሆነ እና ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በጋራ አለመስራቱን በቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

48. ኢንስቲትዩቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በገባው የጋራ የውል ስምምነት ሰነድ መሰረት በኢንስቲትዩቱ ያሉት አመራሮችና ባለሙያዎች በዩኒቨርሲቲው በመገኘት ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ስልጠና እንደሚሰጡ የተቀመጠ ቢሆንም፣

  - በወሎ ዩኒቨርሲቲ ለኮምቦልቻ ካምፓስ መምህራንም ሆነ ተማሪዎች በኢንስቲትዩቱ በኩል ምንም አይነት ስልጠና አለመስጠቱ እና ኢንስቲትዩቱ ካምፓሱ በዘርፉ ስላለበት ክፍተትና ስለሚያስፈልገው ትብብር ድጋፍ/ኦዲት ያደረገበትና ክትትል ያደረገበት ሁኔታ አለመኖሩን፣
  - ኢንስቲትዩቱ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሰጠው ስልጠና አለመኖሩን፣

- ኢንስቲትዩቱ ኮምቦልቻ ካምፓስ በሚሰጠው ኮርሶች ላይ እና የማስተርስና ዲግሪ ፕሮግራም ላይ ያልተሳተፈ ወይም ያልተባበረ መሆኑን፣ ነገር ግን በተግባር ላይ ልምምድ (Apparent Ship) ምደባ ላይ የተወሰነ ትብብር ያደረገ ቢሆንም ትኩረት

የሚያሻው ጉዳዮች ላይ ማለትም የትምህርት ፕሮግራሙ እና የዕውቀት ሽግግሩ ላይ ትብብር ያላደረገ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. ኢንስቲትዩቱ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞች የሰጠውን ስልጠና በተመለከተ በናሙና ተመርጠው የታዩ ተቋማት ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ለኮምቦልቻ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኞች የተሰጠ ስልጠና የሌለ መሆኑን፣ በባህርዳር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸው ነገር ግን ኢንስቲትዩቱ ለጋራ ስራቸው ትስስር መኀልበት ያደረገው አስተዋጽኦ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

50. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተጠናቀቁ የምርምር ስራዎች እንደሌሉት ነገር ግን ከአዲስ አበባ እና ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ጅምር ፕሮፖዛሎች እንዳሉት ገልፀው ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት ጋር ግን የምርምር ግንኙነት እንደሌለው፤ በአጠቃላይ እንደ ተቋም ምርምር ላይ ገና የሚቀረው እንደሆነ እና አቅሙም በመገንባት ሂደት ውስጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የመሰረተውን ኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ፎረም ከመመስረት የዘለለ የተሰራ ስራ የሌለና በታሰበው ልክ ያልተሳሰረ ስለመሆኑ በ2009 ዓ/ም እቅድ ላይም በግምገማ የተቀመጠ መሆኑን፤ ገልጸው በዚህ ግምገማ ላይም ስራው ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ የታመነበት በመሆኑ እንደ ክፍተት ይወሰዳል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

51. የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት አስተያየት

- የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ፎርም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ባወጣው የማደራጃ የህግ ማዕቀፍ መሰረት የተመሰረቱና የኢንስቲትዩቱ ዋና ኃላፊነት ፎረሞቹን መመስረትና በሂደት መደገፍ እንጂ የስራው ባለቤቶች ዩኒቨርስቲዎቹን ጨምሮ የፎረም አባላት መሆኑን፣ የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ፎርም በተመለከተ ከቁርኝት ፕሮግራም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑን፣

- በኢንስቲትዩቱ የሚደረግ ድጋፍ ዩኒቨርስቲዎች/ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች፡ እንዲሰራ የሚጠበቅበትም/ እየሰራ ያለውም የሚዘጋጁ ስርዓተ ትምህርት ምን ምን መያዝ እንደሚገባቸውና የኢንዱስትሪው ፍላጎትና የዕድገት ደረጃ መሰረት በማድረግ አስፈላጊውን ግብዓት መስጠት እንደሆነ፣ ቴክኒክና ሙያ በተመለከተ በተመሳሳይ በየደረጃው (level) መካተት የሚገባቸው ተቋማቶች መሟላት የሚገባቸው ፋሲሊቲ ምክር መስጠት በመሳሰሉት ላይ ኢንስቲትዩቱ እየተሳተፈ መሆኑን፣ የተቋማቶቹን ባለሙያዎች የሚያበቁ ስልጠናዎች እየሰጠ መሆኑ፤ በኢንስቲትዩቱ ሙያተኞች ሊሸፈኑ የማይችሉት ደግሞ በቁርኝት አካሉ ድጋፍ እንዲሰሩ እየተደረገ እንደሆነ፣ መረጃዎች ማየት እንደሚቻል፣

ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም በተላከላቸው በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት

- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉንም አካል የሚያሳትፍበት እና ኢንስቲትዩቱ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን፣ ~~ቢገልጹም ፤~~
- ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት የጋራ የመግባቢያ የስምምነት ሰነድ በ 2008 ዓ.ም እና 24/2010 ዓ.ም በጋራ የሚሰሩ ጥናትና ምርምር ርዕሶችን በተመለከተ የጨርቃጨርቅ ኢንስቲትዩቱ የጻፈው ደብዳቤ ፣ ለደቡብ ክልል ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮ ለማጣቀሻ የሚውል መጽሐፍ ዝርዝር መላካቸውን፣
- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል ጋር በጋራ የሚሰሩበትን ሊገልጽ የሚችል ደብዳቤ ፣ የከፍተኛ ትምህርት የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ንዑስ ቀጠናዊ ትስስር ፎረሞች በ ኮምቦልቻ፣ አክሰም ፣ድሬደዋ ፣ ሀዋሳ ፣ መቀሌ እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ማድረጋቸውን፣ እና
- ኢንስቲትዩቱ በኢንተርንሺፕ ለወሎ/ኮምቦልቻ ዩንቨርሲቲ ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ድሬደዋ ዩኒቨርሲቴ ተማሪዎች ድጋፍ ማድረጉን እና ስልጠና መስጠቱን፣

ገልጸዋል፡፡

52. የሥራ ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ፎርም ከመመስረት ባለፈ በሂደት ስለተደረገው ድጋፍ፣ እስካሁን በተዘጋጁት ሥርዓተ ትምህርቶች ላይ የኢንዱስትሪውን ፍላጎትና የዕድገት ደረጃ መሰረት አድርጎ ስለሰጠው ድጋፍ፣ ቴክኒክና ሙያ በተመለከተ በየደረጃው (level) መካተት የሚገባቸው ተቋማቶች መሟላት የሚገባቸው ፋሲሊቲ ምክር የሰጠ ስለመሆኑ፣ በኢንስቲትዩቱ ሙያተኞች ሊሸፈኑ ያልቻሉት ተለይተው በቁርኝት አካሉ ድጋፍ እንዲሰሩ የተደረጉ ስለመሆናቸው፣ በኦዲቱ ወቅት የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ፣ ተሰጡ የተባሉ ድጋፎች ከቁርኝት ፕሮግራም ጋር በተያያዘ የተሰራ ስራ ስለመኖሩና ወይም ስለሚያገናኘው ማረጃ በለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

53. ኢንስቲትዩቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዘርፉ የሰው ሃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ ተቋማት መካከል፤ ያለው ግንኙነትና ትስስር እንዲያድግ ድጋፍ እና ክትትል ባለማድረጉ እንዲሁም በቁርኝት ፕሮግራሙ ተጠቅሞ ያሰለጠናቸውን ባለሙያዎች የእውቀት ሽግግር ለማድረግ እንዲቻል ዩኒቨርስቲዎች/ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች በሚዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ምን ምን መያዝ እንደሚገባቸው ተሳትፎ አለማድረጉ፣ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ባለማሰልጠኑ፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ ባለመስራቱና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ባለማድረጉ፡ የትምህርት ተቋማቱ በዘርፉ የሚያፈሩት የሰው ሀይል ተግባር ተኮር እውቀት የተላበሱ እንዳይሆኑ እና ፋብሪካዎችም ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል እንዳያገኙ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት የጥናትና ምርምር ስራዎች ስለመካሄዳቸው፣ ውጤቱንም ስለመታተሙ እና ሲምፖዚየም ሰለመዘጋጀቱ፣

54. በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ሊያካሂድና ውጤቱን ሊያሳትም እንዲሁም መደበኛ በሆነና ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲምፖዚየም ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በሁለተኛው አምስት ዓመት 2008-2012 የጥጥ ልማት እና የጨርቃጨርቅ ኢንዳስትሪ ልማት እቅድ ላይ በቂ እውቀት፡ ክህሎት እና ልምድ

ያለው የሰው ኃይል ባለመፈራቱ በዘርፉ የምርምር እና ስርፀት፡ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚጠበቀው ደረጃ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት በኢንስቲትዩቱ በኩል በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ያልተካሄዱ መሆኑን እና በኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ፕሮግራም ሲምፖዚየሞች መዘጋጀቱ ፤ ይሁን እንጂ በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ፕሮግራም ሲምፖዚየም እንዲዘጋጅ በስምምነቱ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

57. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኒፍት ሲምፖዚየም በተመለከተ ከዕቅድ መውጣቱና ምንም የተከፈለ ክፍያ የሌለ መሆኑን፤ ለመታተም የሚበቃ የምርምር እና ጥናት ስራዎችም እንደሌሉ፤ አሁን ባለው ሁኔታ የምርምር ስራዎችን ለማሳተም የሚያበቃ ወርክ ሾፕ እና ፋሲሊቲ ስላልተሟላ በሚፈለገው ሁኔታ እየሄደ እንዳልሆነና የዘርፉ የጥናትና ምርምር ውጤት ስራዎችን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ አቅም በየጊዜው እየተገነባና ሞዴል ፋብሪካዎች በመገንባት ላይ ያለን በመሆኑ በቀጣይ መሰራት ያሚገባቸውና በሂደት የሚሰሩ እንደሆኑ የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

58. የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት አስተያየት በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) የቁርኝት ፕሮግራም ሲምፖዚየም እንዲዘጋጅ ስምምነቱ ላይ ያለ ቢሆንም በስምምነቱ ሰነድ ላይ የክፍያ ስርዓቱ ስላልተቀመጠና ምንም አይነት ለዚህ ተግባር የአገልግሎት ክፍያም ስላልተፈፀመና በቀጣይ በኢንስቲትዩቱ በተፈጠረ በራስ አቅም ማከናወን እንደሚቻል መግባባት ላይ ስለተደረሰ በቁርኝት በኢጋሩ ሲምፖዚየም ያልተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

59. የሥራ ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ

- ይህን ሲምፖዚየሙ እንዲቀርና በራስ አቅም እንዲከናወን ለማከናወን የተደረሰ የውል ማሻሻያ ያልቀረበ ወይንም ስምምነቱን ሊቀይረው የሚችል መግባባት ላይ የተደረሰበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- እንዲሁም በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት እና እንደ ማስረጃ ካቀረቡት የተለያዩ ጥናቶች ውስጥ

- EXPORT MARKETING STRATEGY FOR ETHIOPIAN TEXTILE & APPAREL INDUSTRY (ETIDI-NIFT Twining Arrangement, May, 2017) ከቁርኝት ሮግራም ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ሲሆን፣

ነገር ግን ሌሎቹ ጥናቶች

- AN OVERVIEW OF AMERICAN TEXTILE & APPAREL MARKET ( SEP,2016) ፣ OVERVIEW OF EU MARKET & PRACTICAL MARKET INSITE OF EU (መች እና በማን እንደተዘጋጀ የማይገልጽ)፣
- DOCUMENT FOR AWARENESS CREATION ON COMMON MARKET OF EASTERN & SOUTHERN AFRICA ( DEC, 2015) ፣
- AN OVERVIEW OF EAST AFRICAN TEXTILE & APPAREL MARKET(DEC, 2016)፣ እና
- ASSESSMENT OF EXISTING STATUS & RATING OF ETHIOPIAN GINNING FACTORIES WITH SUPPORT SCHEME RECOMMENDATIONS (AUG,2017)፣

በተለያየ ጊዜ በተለያዩ የኢንስቲትዩቱ ዳይሬክቶሬቶች የተጠኑ ጥናቶች ሲሆኑ ከቁርኝት ፕሮግራሞቹ ጋር ተያይዘው ስለመከናወናቸው ለመረዳት የሚያስችል የሚገልጽ ነገር አልቀረበም፡፡

60. በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ባለማካሄዱ የዘርፉ ሥር የሚገኙ ተቋማትና ፋብሪካዎች ጥናቶቹን እና ምርምሮቹን ለዘርፉ እድገት እንደግብአት ተጠቅመው የምርት ሂደቱን በማሻሻል ተወዳዳሪ ለመሆን የሚረዳ ግብዓት እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

**በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት በማካሄድ ድጋፍና የምክር አገልግሎት ስለመሰጠቱ፣**

61. ኢንስቲትዩቱ በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት በማካሄድ የቴክኒካል ድጋፍና የምክር አገልግሎት ሊሰጥ እና ጥናታዊ ስራዎችን ሊተገብር ይገባል፡፡

62. በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት በማካሄድ የቴክኒካል ድጋፍና የምክር አገልግሎት ሊሰጥ እና ጥናታዊ ስራዎችን ሊከናወን እንደሚገባ

Providing technical support and conducting research activities in Apparel Manufacturing, Marketing and Product development through two joint research in selected areas and providing technical support and Consultancy services through two joint consultancies in selected areas (page 9 of 26, 6.4 & 6.5) ኢኒስቲትዩቱ ከናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ከተባለው የቁርኝት አጋር በገባው የስምምነት ሰነድ ላይ ተገልጿል፡፡

63. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ ፋብሪካዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ኢንስቲትዩቱ ያስጠናው ጥናት ስለመኖሩ የማያውቁ መሆናቸው እና ጥናትም እንዳልደረሳቸው በጥናቱ ላይ የተመሰረተ ድጋፍና የምክር አገልግሎት እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

64. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ እና በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት ምላሽ እና በቀረበ ማስረጃ ጥናት ተጠንቶ በጥናቱ መሰረት ድጋፍ እየተደረገ ቢሆንም ፋብሪካዎች ግን ተወዳዳሪ የማይሆኑበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቀረበልን ማስረጃ የሚያሳየው የክፍተት የተለየበት/መለያ ሰነድ እንጂ በተመረጡ ፋብሪካዎች በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት የተጠና የገበያ ጥናት ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65. ኢንስቲትዩቱ በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት ባለማከናወኑ እና ለአምራቾች ጥናቱን ባለማሰራጨቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያደርገው ድጋፍ ጥናት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ለአምራቾች የሚሰጠው የገበያ ድጋፍ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

### የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤

66. ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ሊደግፋቸው ይገባል፡፡

67. የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ መደረግ እንዳለበት (Forcasting the

global market dynamics and preparing the Ethiopian Apparel sector to meet the changing reqourments.) ኢኒስቲትዩቱ በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFTpage 9 of 26, 6.6 and page 7 of 11, # 14) የቁርኝት አጋር ጋር በገባው የስምምነት ሰነድ ላይ ተቀምጧል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ ፋብሪካዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በኢንስቲትዩቱ የተሰራ የገበያ ትንበያ ስለመኖሩ የማያውቁና የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉም የተደረገላቸው ድጋፍ የሌለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

69. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የወደፊት የገበያን ሁኔታ እና ተያያዥነት ያላቸው ድጋፎች በተመለከተ በአጠቃላይ በአቅም ግንባታ ስልጠና እንደሚዳሰሱ፣ export development የሚል ጥናት፣ strategic document መዘጋጀቱን እና ገና ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት በማድረግ ወደ ሥራ የሚገባ እንደሚሆን እንዲሁም ፋብሪካዎች አለም አቀፍ የገበያ ጉባኤዎች ላይ እንዲካፈሉ ያደረጉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

70. በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት እና በቀረበ ማስረጃ የቁርኝት ፕሮግራሙም ዓላማ የተቋሙን አቅም መገንባት በመሆኑ በዚህ ረገድ በስምምነቱ በተቀመጠው መሠረት

- የዘርፉ በቀጣይ 10 ዓመታት ሊመራበት የሚችል የኤክስፖርት ገበያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡
- በአፍሪካ ገበያ ላይ ጥናት ተከናውኗል፣
- በተጨማሪም የእውቀት ሽግግርን በሚያረጋግጥ መልኩ ገበያ ትንበያ እና የምርት ልማትና ትንበያ ላይ የሥልጠና ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በዚሁ መሠረትም የስልጠና ጥሪ ተላልፎ ለፋብሪካ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት የስልጠና ጥሪ የተደረገባቸው ደብዳቤዎች እና የሰልጣኞች አቴንዳንስ ሰነዶችን መመልከት ይቻላል:
- ለኢንስቲትዩቱ በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) በኩል በተላለፈ የዕውቀት ሽግግር በኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በመርቸንዳይዚንግና ተዛማጅ ርዕሶች ላይ ለፋብሪካዎች ተግባር ተኮር ስልጠናና ምክር እየተሰጠ ይገኛል

የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

71. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በቁርኝት ስምምነቱ በተቀመጠው መሠረት በተዘጋጀው የዘርፉ ፋብሪካ በቀጣይ 10 ዓመታት ሊመራበት የሚችል የኤክስፖርት ገበያ ስትራቴጂ ጥናት  መሰረት ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በገበያ ትንበያ ጋር በተያያዘ የተሰራ ስራን ሊገልጽ የሚችል ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም የቁርኝት ፕሮግራሙም ዓላማ የኢንስቲትዩቱን አቅም መገንባት ብቻ ባለመሆኑ በNIFT እና ICT የቁርኝት ስምምነት ሰነድ ላይ ፋብሪካዎች በቁርኝት ፕሮግራሙ ተደራሽ መሆን ያለባቸው በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል አልተቻለም፡፡

72. ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ ባለመስራቱ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዳያሟሉ እና ተወዳዳሪ ምርት አምርተው አድማሳቸውን እንዳያሰፉ ያደርጋቸዋል፡፡

## በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ላለው የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና ስለመስጠቱ እና ድጋፍና ክትትል ስለማድረጉ፣

73. ኢንስቲትዩቱ ከኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ጋር በተገባው ስምምነት መሰረት በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያለውን የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና በመስጠት በማደግ ላይ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች እንዲደግፍ ክትትል ሊያደርግ (Support the industry in developing its human resources at managerial, technical and skilled workforce levels by providing specialized trainings (ICT, page 6 of 21) እና ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ

- ኢኒስቲትዩቱ የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅሙን በሚፈለገው ደረጃ ፈጥኖ አለመገንባቱ፣
- ስልጠናዎች በዕቅድ መሰረት ያለመከናወናቸው፣
- ስልጠና የሚሰጡ የቁርኝቱ ባለሙያዎች በወቅቱ ያለመገኘት፣
- ኢኒስቲትዩቱ በወቅቱ ክፍያ ያለመፈጸም ችግሮች መኖራቸውን

በሁለተኛው አምስት አመት 2008-2012 የጥጥ ልማት እና የጨርቃጨርቅ እንዳስትሪ ልማት እቅድ፣ የኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) የቁርኝት

ፕሮግራም አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የግምገማ ቃለ ጉባኤ ነሀሴ 26/2007 ዓ/ም እንዲሁም progresive report of the streeng comittee of ICT and progresive report of NIFT ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

75. በናሙና በታዩ ቪሊጅ ኢንዱስትሪ፣ ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና ዲኤች ገዳ የአክላሪክ ማቅለሚያ ፋብሪካ ኃላፊዎች ለቀረበ ጥያቄ የሠጡት ምላሽ በኢንስቲትዩቱ ምንም የተሰራ ክትትል እና የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳብ ወይም ግብረ-መልስ የሌለ መሆኑን፣ በባህርዳር ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር የሥራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ ለሰጡት ምላሽ በ2008 ዓ.ም ለ7 ቀናት በglobal sourcing for apparel & textile industry በ2009 ዓ.ም ለ9 ቀናት quality evaluation of textile material ከተሰጠ ስልጠና ውጪ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

76. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ

- ስልጠናን ተደራሽነት በተመለከተ ከነባራዊ ሀብት (resourse) አኳያ የሚታይ ሲሆን ፋብሪካዎች እንደሚፈልጉት ባይሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ የስልጠና አሰጣጡ በመሻሻል ላይ የሚገኝ መሆኑን፣
- የክትትል ስራ ላይ ግን ክፍተት ያለ መሆኑን ለዚህም የአሰራር ስርአት (system) መዘርጋት እንዳለባቸው፣ በቁርኝት ስምምነት መሰረት ምንም እንኳን ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) በተለያዩ በተጠቀሱት ፕሮግራሞች የኢንስቲትዩት አመራርም ሆነ ባለሙያዎችን አቅም የማሳደግ ስራ እየሰራና ለኢንዱስትው የሚደረገው ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ የመሻሻል ሂደት ላይ ያለ ቢሆንም ውስንንት የለውም ብለን ግን አንወስድም፣
- የአቅም ግንባታ በአንድ ጊዜ ፍፁምነት /Perfection/ ላይ ሊደረስ እንደማይቻል፣ በኢንስቲትዩቱ በኩል የሚሰጡ ስልጠናዎች ለፋብሪካው ምን እሴት እንደጨመረለትና ያመጣውን ፋይዳ መመዘን ያለበት በዋናነት ባለሀብቱ መሆን እንዳለበት፣
- በምርትና ምርታማነት በኤክስፖርት አፈፃፀምና የመሳሰሉት ኢንስቲትዩቱ በኩል ሊሰራ የሚችለው የወረቀት ስራ መሆኑን፣
- በፋብሪካ ተሰማርተው ያሉ ሠራተኞች እውቀትና ክህሎታቸው እያደገ ሲሄድ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ እንዳለም መታየቱና ይህ አንዱ የስልጠናው ውጤታማነት ከሚታይባቸው መንገዶች መካከል የሚመደብ መሆኑ፣

- በባለሀብቱ የተጠየቁ ስልጠናዎችን ሁሉ ደግሞ ለባለሀብቱ ይሰጣሉ ማለት እንዳልሆነ፣ ባለሀብቱ በራሱም ሊያሟላ የሚገባው ነገር ሊኖር እንደሚገባ፣
- የቁርኝት ፕሮግራም አካላት እያንዳንዱን ፋብሪካ እየተዘዋወሩ የሚሰሩበት የስምምነት አግባብ እንደሌለው እና ለኢንዱስትሪ አግባብነት የሌለው እንደሆነ ለቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እንዲሁም በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በሚደረገው የቁርኝት የስልጠና ፕሮግራሞች (hand holdings) በሴሚናር እና ኮንፈረንስ እዲሁም የተለያዩ የሪፍሬሽር ኮርሶች ስልጠና በሚከናወኑ ስራዎች የፋብሪካው ባለሙያዎች በሂደቱ የስልጠና አገልግሎት ሊያገኙ እንዲችሉ የተመቻቸበት ሁኔታ መኖሩና ለወደፊትም እንደሚመቻች ገልፀዋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በኢንስቲትት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ፕሮግራም አማካኝነት የሚተላለፈውን የአቅም ግንባታ ለመቀበል የአቅም ውስንነት እንደሌለው ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በውጭ አገር የሚሰጡ ስልጠናወችን በተመለከተ በዕቅዱ መሰረት ያለመከናወናቸው ምክንያት ስልጠናውን የሚሰጡ ባለሙያዎች በወቅቱ ስለማይገኙ እና በኢንስቲትዩቱ እንደ ሀገር ካለው በውጭ የምንዛሬ እጥረት ምክንያት ክፍያ በወቅቱ መፈፀም ስላልተቻለ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

77. የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች የሰጡት ምላሽ እንዳለ ሆኖ የቁርኝት ፕሮግራም አጋሮች በፋብሪካዎች እየተንቀሳቀሱ/እየተዘዋወሩ የሚሰሩበትና የሚከታተሉበት የስምምነት አግባብ አይደለም የተባለው ፋብሪካዎች በቁርኝት ፕሮግራም በቀጥታ በሥልጠና ሊደገፉ እንደሚገባ በNIFT እና ICT ስምምነት ሰነድ ላይ (Support the industry in developing its human resources at managerial, technical and skilled workforce levels by providing specialized trainings (ICT, page 6 of 21) and (NIFT, activities on page 7 of 11) የተጠቀሰ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

78. ኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ፕሮግራሙ በገባው ስምምነት መሰረት በማደግ ላይ ላሉ ኢንዱስትሪዎች በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያሉትን የሰው ሀብቶች ልዩ ልዩ ስልጠና በቁርኝት አጋሩ መሰጠቱን ባለመከታተሉ፣ ሊደግፍ እና ሁኔታዎችን ሊያመቻች ባለመቻሉ ኢንዱስትሪዎቹ ከቁርኝት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ

እንዳይሆኑ እና ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዳይሆኑ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

**በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች የተዘጋጁ፣ ሥርዓተ-ትምህርቶች የተቀረጹ፣ ለአጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ማንዋሎች እና ሞጁላር ኮርሶች ስለመዘጋጀታቸው፣**

79. ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች ሊያዘጋጁ እና ሥርዓተ-ትምህርቶች ሊቀርፅ እንዲሁም ለአጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች የሚሆኑ ማንዋሎችን እና ሞጁላር ኮርሶችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጥር 2007 ዓ.ም ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) የቁርኝት አጋር በተገባው ስምምነት ሰነድ በየአመቱ የሚዘጋጅ ስድስት የስልጠና እና ልዩ እቅድ ማውጫ ሞጁል እንደሚዘጋጅ የተገለጸ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

81. ስለሁኔታው ለወሎ ዩኒቨርሲቲ ኮምቦልቻ ካምፓስ የሚመለከታቸው ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የሚስማሙ ባለሙያዎችን በማሰማራት በሚቀረጽ ካሪኩለምና ሥርዓተ ትምህርት ላይ አስተያየት እንደሚሰጡና በጋራም የተሰራበት ሁኔታ እንደነበር፣ ነገር ግን የኮርስና ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ መሳተፍ ቢኖርባቸውም እንዳልተሳተፉ ገልፀዋል፡፡

82. ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር ፖሊ ቴክኒክ ኢኒስቲትዩት እና ለኮምቦልቻ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ በተጨባጭ የቀረጸው ወይም ያቀረበው ካሪኩለምም ሆነ ሞጁላር ኮርስ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

83. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሁሉንም የስልጠና materials ከresource እጥረት አኳያ የሚከብድ ቢሆንም በርካታ የስልጠና ማንዋሎች ያሉን ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ለሰልጣኞች hard copy አዘጋጅተን እንሰጣለን እንደ አስፈላጊነቱም soft copy የምንሰጥበት ሁኔታ አለ፣ ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከሞጁላርና ማኑዋል ባለፈ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ግብዓቶችንም የሚሰጡበት ሁኔታ እንዳለ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

84. በተጨማሪም በቁርኝት አጋሩ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ተምረው በመጡና በሰለጠኑ የኢንስቲትዩ የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ሞጅሎቹን የማዘጋጀት አቅም መፈጠሩ ስለተረጋገጠ ከፕሮግራሙ እንዲወጣ መደረጉንና ለዚህ ተግባር የተከፈለም ሆነ ሊከፈል የሚገባ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡

85. በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ እና በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የኮርስ ዝግጅት በተመለከተ ለምን እንዳልተሰራ ምላሽ አልሰጡም፡፡ ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች ባለማዘጋጀቱ፣ ሥርዓት-ትምህርቶች ባለመቅረጹ እንዲሁም ሞጁላር ኮርሶችን ባለማዘጋጀቱ በዘርፉ የሰው ኃይል ልማት እና እድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በቁርኝት ስምምነቱ መሰረት ለዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ ክትትል ስለማድረጉና ስለማመቻቸቱ፣

86. ኢንስቲትዩቱ በቁርኝት ስምምነቱ መሰረት ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) የተባለው አጋር ድርጅት ለዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ከልብስ ቴክኖሎጂ፣ ከግብይት፣ ከገበያ ትንተና እና ከዘርፉ የአስተሳሰብ ችሎታ (Intelligence)፣ ትንበያ (Forecasting)፣ የምርት ዕድገት ጋር ግንኙነት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ ክትትል ሊያደርግ እና ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ የቁርኝት አጋሩ (NIFT) ጎንደር ላይ በቢዝነስ እቅድ እና በገበያ ትንበያ ዙርያ እንደሰራ ቢገለጽም፤ በልብስ ቴክኖሎጂ፣ በግብይት፣ በገበያ ትንተና እና በዘርፉ የአስተሳሰብ ችሎታ (Intelligence)፣ እንዲሁም የምርት እድገት ዙርያ በጊዜ ማነስ ምክንያት ስልጠና እንዳልተሰጠ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) በኦዲቱ ወቅት ለቀረበለት ጥያቄ በተሰጠው ምላሽ ላይ ተገልጿል፡፡

88. እንዲሁም ለባህርዳር ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ለቀረበ ጥያቄ በተሰጠው ምላሽ በ 2008 ዓ.ም ለ 7 ቀናት በ global sourcing for apparel & textile

industry በ 2009 ዓ.ም ለ 9 ቀናት quality evaluation of textile material የተሰጠው መሆኑን ከዚህ ሌላ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

89. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቁርኝት ፕሮግራም ስምምነቱ በተቀመጠው መሠረት ዘርፉ በቀጣይ 10 ዓመታት ሊመራበት የሚችል የኤክስፖርት ገበያ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን፣ በተጨማሪም የእውቀት ሽግግርን በሚያረጋግጥ መልኩ ገበያ ትንበያ እና ምርት ልማት ረገድ የሥልጠና ማኑዋል ተዘጋጅቶ በዚሁ መሠረትም የስልጠና ጥሪ ተላልፎ ባለሙያ ለላኩ ፋብሪካዎች ስልጠና እንደተሰጠ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የሰጡት አስተያየት በ ቦሌ ለሚ ፣ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ (25000 ለሚሆኑ) እና በተለያዩ ፋብሪካዎች ቅጥር ግቢ የአምራቾችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ስልጠና መስጠታቸውን ገልጸዋል፡፡

90. የሥራ ኃላፊዎቹ ይህንን ቢሉም

- በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) የተባለው የቁርኝት አጋር በልብስ ቴክኖሎጂ፣ በግብይት፣ በገበያ ትንተና እና በዘርፉ የአስተሳሰብ ችሎታ (Intelligence)፣ እንዲሁም የምርት እድገት ዙርያ በጊዜ ማነስ ምክንያት ስልጠና አለማከናወናቸውን በመግለጻቸው፣

የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

91. ኢንስቲትዩቱ በስምምነቱ መሰረት NIFT የተባለው አጋር ድርጅት ለዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ከልብስ ቴክኖሎጂ፣ ከግብይት፣ ከገበያ ትንተና እና ከዘርፉ የአስተሳሰብ ችሎታ (Intelligence)፣ ትንበያ (Forecasting)፣ የምርት ዕድገት ጋር ግንኙነት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ ክትትል ባለማድረጉ እና ሁኔታዎችን ባለማመቻቸቱ ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪና ውጤታማ መሆን እንዳይችሉ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

### በቁርኝት ፕሮግራሙ ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎች እና ዘዴዎችን መነደፋቸውን በተመለከተ፤

92. ኢንስቲትዩቱ ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን እና ዘዴዎችን እንዲነድፍ ክትትል ሊያደርግ እና ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኢኒስቲትዩቱ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር እቅድ 2008- 2012 የተጠናከረ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን እና የክትትል ስራ አለመከናወኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ ያደረገው ሙከራ ቢኖርም በጊዜ እጥረት ምክንያት ያልተሰራ መሆኑን ለኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) የቁርኘት አጋር ለቀረበ ቃለ መጠይቅ የተሰጠ ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

94. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ እንደ ተቋም ስራችን ሲሆን እንደ ቁርኘት ፕሮግራም (ICT) ግን የሚያገናኘው ነገር አይኖርም፤ የቁርኘት ፕሮግራም ውለታ የራሳችንን ተቋም አቅም መገንባት ነው፤ እንደተቋም ከውጪ በዘርፉ ለመሳተፍ የሚመጡ ባለሃብቶችን ተቀብለን መረጃዎችን በመስጠት አስፈላጊውን ትብብር እያደረግን ነው፤ እንዲሁም የዘርፉን የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ስራ እንደ አገር የኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሰራ በመንግስት የስራ አቅጣጫ ስለተሰጠና በዚህ የስራ ኃላፊነትም ተቋሙ በህግ ስለተደራጀ የቁርኘት አጋሩ በዚህ ረገድ ስራዎች እንዲሰራ ወይም አቅማችንን እንዲገነባ አይጠበቅበትም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ እና በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት በኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጅዎችንና ዘዴዎችን ያልተነደፉ እና ይህንንም ስራ እንዲሰራ ያልተጠበቀበት የቁርኘት ትግበራ የፈጠረበት የተቋማችን የስራ ክፍል የስራ ሃላፊነቶች መዘርዝር ያልተጠቀሰ ከመሆኑ አኳያ ይህ ስራ ለማከናወን የቁርኘት አጋሩ ሃላፊነት እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትየዩቱ ኃላፊዎ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም በከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT)ጋር ኢኒስቲትዩቱ የገባው የስምምነት ሰነድ ላይ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

95. ኢንስቲትዩቱ የቁርኘት አጋሩ (ICT) ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን እና ዘዴዎችን እንዲነድፍ ክትትል ባለማድረጉ እና ሁኔታዎችን ባለማመቻቸቱ የዘርፉ ኢንቨስትመንት እንዳያድግ ያደርገዋል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ የኢንስቲትዩቱ እና የዘርፉ ኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ማመቻቸቱን በተመለከተ፤**

96. ኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ሊያመቻች ይገባል፡፡

97. የኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እንደሚደረግ እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ የሚደረግበት አቅም Enable ETIDI's chemical and environmental laboratories be accredited and have the capacity to facilitate the sertefication of industry laboratories (ICT, page 6 of 21) ለኢንስቲትዩቱ እንደሚፈጠር ከኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) የቁርኝት አጋር የተገባው ስምምነት ሰነድ ላይ ተገልጿል፡፡

98. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች የማረጋገጫ ወረቀት አለማግኘታቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ አለመደረጋቸው፣
- እንዲሁም በየፋብሪካዎች ያሉ ላብራቶሪዎች እውቅና እንዲያገኙ ያልተሰራ መሆኑን

በ05/12/08 በኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ ሽግግርና ምርምር ላብራቶሪ ከተደረገ ቃለ ጉባኤ፣ ከ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

99. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ እንደ አገልግሎት ሰጪ እና እንደመንግስት ተቋም ኢንስቲትዩቱ በላቦራቶሪዎች certified መሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም አሁን ላይ በፊዚካል እውቅና ያገኘ ሲሆን በኬሚካል እና በአካባቢ ላብራቶሪ እዉቅና ለማግኘት በሂደት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

100. የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የፋብሪካዎች የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖረው ዕውቅና እንዲያገኝ አይጠበቅበትም፤ የኢንስቲትዩቱ ላብራቶሪ ግን አገልግሎት ሰጪ ተቋም

እንደመሆኑ መጠን ዕውቅና ስለሚያስፈልገው ይህ ሁኔታ ደግሞ ሂደትና ጊዜ የሚፈልግና ከስርዓት ዝርጋታና ከሰው ሀብት ልማቱ ባሻገር የመሰረት ልማቶች ማሟላት የሚጠይቅ በመሆኑ መሰረተ ልማቱን በመንግስት በሚመድበው ውስን በጀት ለማሟላት እየተሰራ ሲሆን የስርዓት ዝርጋታውና የሰው ሀብት ልማቱ ግን በቁርኝት አጋር ድጋፍ እየተደረገለት ያለና በቀጣይ ለሚከናወን የዕውቅና የማግኘት ሂደት ውስጥ አጋዥ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ እና በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በሰጡት የፅሁፍ አስተያየት ስለ ኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላብራቶሪ ዙርያ ሀሳብ አልሰጡበትም፡፡ የፋብሪካዎች የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖረው ዕውቅና እንዲያገኝ አይጠበቅበትም ያሉ ቢሆንም በICT የስምምነት ሰነድ ላይ በመገለጹ ምላሹ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

101. ኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ባለማመቻቸቱ የዘርፉ ምርትና ምርታማነት ጥራት እድገት እንዳይፋጠን፣ ተወዳዳሪና አለም አቀፍ ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርገዋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር መሰረት ስለመፈጸሙ መከታተሉን እና መገምገሙን በተመለከተ፣

102. ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ሊከታተል እና ሊገመግም እንዲሁም የፕሮግራሙ ትግበራ በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ረገድ ያመጣውን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡

103. ይሁን እንጂ የቁርኝት ፕሮግራም ዝርዝር እቅድ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት እየተፈጸመ አለመሆኑ፣ ቁርኝት ፕሮግራም የተገኘውን አቅም ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ፣ ከቁርኝት ፕሮግራም ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች መካከልም የአቅም ክፍተት ያለበት መኖሩ እና ከቁርኝት ፕሮግራሙ የመጡ ባለሙያዎች የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች የሚሰሩትን ሲሰሩ ማለትም የተለየ ለመስራት አቅም የሌላቸው መሆኑ፣ስራዎችን በየጊዜው እየገመገሙ መሄድ ላይ ክፍተት እንዳለ በማኔጅመንትና በማኔጅመንትና በቁርኝት የተማሩ ባለሙያዎች ጋር በተደረገ ስብሰባ 18/07/09፣ 21/03/09፣18/07/09 ተገልጿል፡፡

104. እያንዳንዱ የቁርኝት ፕሮግራም በተናጠል ሲታይ

**በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ፕሮግራም፡-**

- በረዥም ስልጠና ወይም ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት በማስተር ኦፍ ፋሽን ማኔጅመንት አስራ ሁለት የኢንስቲትዩቱ የሰው ሃይል እንደሚጋበዙ በስምምነት ሰነዱ ተቀምጧል፡፡
- በ"Continuing Education Programs" (CEP) ለኢንስቲትዩቱ ለሃያ የሰው ሃይል ስልጠና እንደሚሰጥ በስምምነት ሰነዱ ተቀምጧል፡፡
- ወጪን በተመለከተ ለከፍተኛ ትምህርት (ሁለተኛ ዲግሪ) በአሜሪካ ዶላር ዕቅድ 515,808 አፈጻጸም 1,007,084 ፤ በአጭር ጊዜ ስልጠና ዕቅድ 182,970 ክንውን 238,151.26 በተደረገው የኮንትራት ማሻሻያ መሠረት የተከናወነ መሆኑ የገለጹ ሲሆን ተደረገ የተባለው የኮንትራት ውል ማሻሻያ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡
- ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) የተባለው አጋር ድርጅት ለኢንስቲትዩቱ ተስማሚ የሆነ የአስተዳደር ስርዓት እንዲዘረጋለት በስምምነት ሰነዱ ላይ የታቀደ ቢሆንም በጊዜ ማነስ ምክንያት በሚል ያልተተገበረ መሆኑ ለቁርኝት አጋሩ በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ መቻሉ፣

ይሁን እንጂ በረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ወቅት በሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

- የሁለተኛ ድግሪ ዕቅድ ከ12 ወደ 26 ከፍ መደረጉ እና 16ቱ ትምህርታቸውን አጠቃለው የተመለሱ ሲሆን 10ሮቹ ገና በመማር ላይ መሆናቸው፡፡ የሶስተኛ ድግሪ ትምህርት ዕቅድ 3 የነበረ ቢሆንም በተደረገው የኮንትራት ውል ማሻሻያ መሠረት ወደ ሁለተኛ ድግሪ የተቀየረ እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም ተደረገ የተባለው የውል ስምምነት ማሻሻያ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በ"Continuing Education Programs" (CEP) ለአስር ሰው ለአንድ ሴሚስቴር (አራት ወራት) ለቀሪዎቹ አስር ሰዎች ደግሞ ለሁለት ሴሚስቴር (ስምንት ወራት) የሚቆይ ስልጠና መሰጠቱ የተገለጸ ሲሆን ሥልጠናው የተሰጠ ስለመሆኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ ከመሆኑ ባሻገር በፕሮግራሙ በህንድ ለሚገኙ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች

ከስራ ሰዓት ውጪ የሚሰጡት መደበኛ የስልጠና ፕሮግራም መሆኑን በመገንዘባችን ይህን ስልጠና በማሻሻል የሁለተኛ ድግሪ ማስተማር ከተቻለ እና አቅማቸውን እንዲገነቡ ከተደረገ CEP በራሳችን ሙያተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ እንዲታጠፍ መደረጉን በመግለጽ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) ፕሮግራም ስምምነት ሰነድ እና ከኢንስቲትዩቱ ከቀረቡት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

**በኢንዲያን ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) ፕሮግራም፡-**

- በIIT ደልሂ ላይ በቴክኒካል ስልጠና በየአመቱ አምስት የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በአጠቃላይ በሶስት አመት ውስጥ ደግሞ አስራ አምስት የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች እንደሚሰለጥኑ በስምምነት ሰነዱ ላይ ተቀምጧል፡፡
- በIIT ደልሂ ላይ በሊደርሽፕ ትሬይኒንግ በየአመቱ ስድስት የሰው ሃይሎች በአጠቃላይ በሶስት አመት ውስጥ ደግሞ አስራ ስምንት የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች እንደሚሰለጥኑ ተቀምጧል፡፡
- እንዲሁም በአጭር ስልጠና አስራ አራት ባለሙያዎችና ስድስት የስራ ሃላፊዎች እንደተሳተፉ፣ ሰባት ባለሙያዎች የማስተርስ ትምህርት እንዳጠናቀቁና ስምንት ባለሙያዎች ደግሞ ገና የማስተርስ ትምህርታቸው እየተከታተሉ እንደሆነ በኢንስቲትዩቱ ቢገለፅም ማስረጃው ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣

ይሁን እንጂ በተላከው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የተሰጠው ምላሽ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

- የቴክኒካል ስልጠና ዕቅድ 15 አፈጻጸም 14 በ አሜሪካን ዶላር ዕቅድ 105,150 የአፈጻጸም ወጪ 73,900 በቁጥር ከፍተኛ አፈጻጸም የተመዘገበው የቁርኝት አጋር ተቋሙ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር በ 2 ዓመት ለ10 ባለሙያዎች በተያዘ የስልጠና በጀት 14 ባለሙያዎችን ማሰልጠን በመቻሉ እና የ3ኛ ዙር ስልጠና በያዝነው ዓመት ሃምሌ ድረስ የሚሰጥ መሆኑን
- በተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የሰጡት ምላሽ በማኔጅመንት ስልጠና ዕቅድ 18 አፈጻጸም 6 መሆኑና ወጪን በተመለከተ በአሜሪካን ዶላር ዕቅድ 123,870 አፈጻጸም 41,290 የአመራር ስልጠና በቁርኝቱ የመጀመሪያ

ዓመት ብቻ የተከናወነ መሆኑ፤ 2ኛ እና 3ኛ መርሃ ግብር በአገልግሎት ክፍያ መዘግየት ምክንያት ያልተከናወነ ሲሆን ያለፈውን ዓመት ጨምሮ በያዝነው ዓመት የሚከናወን መሆኑን፡፡

- ለ2ኛ ዲግሪ ዕቅድ 21 አፈጻጸም 15 (ይህም ሊሆን የቻለው አንድ ባለሙያ ምዝገባ ለማካሄድ የመጀመሪያ ዲግሪ የመመረቂያ ነጥብ 2.75 እና ከዚያ በላይ ሊኖረው ስለሚገባ)፤ በ አሜሪካን ዶላር ዕቅድ 598,500 አፈጻጸም 202,374 በቁጥር በፋይናንስ አፈጻጸም መካከል የታየው ልዩነት ምክንያት በከፍተኛ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ከሆኑ 15 ባለሙያዎች ውስጥ ትምህርታቸውን ላጠናቀቁ 7 ባለሙያዎች ብቻ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑና ለቀሪ 8 ባለሙያዎች ከ 1 እስከ 2 ዓመት የሚሆን የትምህርት ወጪ በክፍያ መዘግየት ምክንያት ስላልተፈጸመ ነው ( የ 2 ባለሙያዎች የ 1 ዓመት የ6 ባለሙያዎች የ2 ዓመት ክፍያ ያልተከፈለ) ፤ እንዲሁም በማስረጃነት በ 2ኛ ድግሪ ከተማሩት ውስጥ የ 7 ባለሙያዎች ሰርተፍኬት የቀረበ መሆኑ፡፡

በኢንዲያን ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (IIT) ፕሮግራም ስምምነት ሰነድ እና ከኢንስቲትዩቱ ከቀረቡት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

**በኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ፕሮግራም፡-**

- በየአመቱ አንድ እና በአጠቃላይ በሶስት አመት ውስጥ ሶስት የሰው ሀይሎች የሶስተኛ ዲግሪ (ፒ ኤች ዲ ትምህርት) እንደሚያገኙ በስምምነት ሰነዱ ተገልል፡፡
- በቡድን መሪነት ደረጃ ላሉ ባለሙያዎች በመጀመርያው አመት አራተኛው ሩብ አመት፣ በሁለተኛው አመት በሶስተኛው ሩብ አመት እና በሶስተኛ አመት በሁለተኛው ሩብ አመት በአድቫንስድ ስልጠና ህንድ ውስጥ እንደሚሰጥ የተገለፀ ቢሆንም ስልጠናው ስለመሰጠቱ ማስረጃው ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በመካከለኛ አመራር ደረጃ የአስራ አምስት ቀን ስልጠና ስድስት የሰው ሃያሎች፤ እንዲሁም የሁለት ወር የአጭር ጊዜ ስልጠና በሁለት ዙር ስምንት ባለሙያዎች እንደተሳተፉ በኢንስቲትዩቱ ቢገለፅም የዘጠኝ ሰራተኞች ሰርተፍኬት ብቻ የቀረበ መሆኑ፤

ይሁን እንጂ በተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ነው፡-

- በ3ኛ ዲግሪ ዕቅድ 3 አፈጻጸም 1 ቢሆንም በሥራ ክፍሉ የለ2ኛ ዲግሪ ባለሙያ ባለመኖሩና ለ3ኛ ዲግሪ ፕሮግራም ቅድመ ሁኔታ ስለሆነ ሁለቱ የሦስተኛ ዲግሪ ወደ አራት የ2ኛ ድግሪ የተቀየረ መሆኑ ቢገለጽም ውሉ ስለመሻሻሉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣ ወጪ በ አሜሪካን ዶላር ዕቅድ 170,952 አፈጻጸም 56,984 መሆኑ፡፡
- በአጭር ጊዜ ስልጠና በቴክኒካል ባለሙያ ዕቅድ 22 አፈጻጸም 8 ወጪ በአሜሪካን ዶላር ዕቅድ 101200 አፈጻጸም 36800፣ እንዲሁም በማኔጅመንት ስልጠና ዕቅድ 9 አፈጻጸም 7 ፣ ወጪ 41760 አፈጻጸም 32480 ፣ 9 የ አጭር ጊዜ ስልጠና የወሰዱበት ሰርተፍኬት እንደ ማስረጃ የቀረበልን ቢ ሆንም በውጪ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የስልጠናው ቅድመ ክፍያ በኢንስቲትዩቱ በኩል በወቅቱ ያልተፈጸመ መሆኑ፡፡
- ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት በሶስት ዙር አስራ አራት ባለሙያዎች እንደተሳተፉ የተገለጸ ቢሆንም በተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የሰጡት አስተያየት ለ2ኛ ዲግሪ ዕቅድ 9 አፈጻጸም 14 ፣ ወጪ በአሜሪካን ዶላር ዕቅድ 260,928 አፈጻጸም 405,888 ፣ 5 ተጨማሪ 2ኛ ትምህርት የተከናወነው ሁለቱ የ3ኛ ዲግሪ ወደ አራት የ2ኛ ዲግሪ እና በሁለተኛ መንፈቅ ዓመት በስራ ላይ ያልዋለው በጀት ማለትም የ Resident Expert Mandy በመቀነስና ለኮንፍረንስ (Technical Seminar) ሥራ የተመደበ በጀት ለ አንድ የከፍተኛ ትምህርት እንዲማር መወሰኑ እንዲሁም ከ 14 2ኛ ዲግሪ ተምረው ካጠናቀቁት ውስጥ የ 5ቱ ብቻ ሰርተፍኬት እንደ ማስረጃ የቀረበልን መሆኑ፡፡

በኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ፕሮግራም ስምምነት ሰነድ እና ከኢንስቲትዩቱ ከቀረቡት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የሦስቱን ፕሮግራም የተፈቀደ በጀት እና የወጣው ወጪ በአሜሪካን ዶላር ሲገለጽ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

| ፕሮግራም | አጠቃላይ የተፈቀደ በጀት | አጠቃላይ ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ | አጠቃላይ ስራ ላይ ከዋለው ውስጥ ለት/ትና ስልጠና | ከአጠቃላይ ስራላይ ከዋለው ት/ትና ስልጠና ሲቀነስ (ሌሎች ወጪዎች) |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | የወጣው ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|
| NIFT | 4,263,440.08 | 3,079,712.87 | 72.2% | 1,245,235.26 | 1,834,477.61 |
| ICT | 1,998,665.00 | 1,131,127.60 | 56.6% | 532,152.00 | 598,975.60 |
| IIT | 1,059,870.00 | 349,246.02 | 33% | 317,564.00 | 31,682.02 |
| ድምር | 7,321,975.08 | 4,560,086.49 | 62.3% | 2,094,951.26 | 2,465,135.23 |

ከላይ በተገለጸው መሰረት

- ፕሮግራሙ በተያዘለት የጊዜ ገደብ NIFT ሰኔ 2010 ዓ.ም ፣ ICT ጥር 2010 ዓ.ም እና IIT ሀምሌ 2010 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን ከአጠቃላይ ከተመደበው በጀት ስራ ላይ የዋለው ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ 62.3 ከመቶ በመሆኑ ከጊዜ ገደብ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ
- ስራ ላይ ከዋለው አጠቃላይ ወጪ ለትምህርትና ስልጠና በቀረበልን ጥቅል መግለጫ ማስረጃ መሰረት ወጪ 45.9 ከመቶ የሚሸፍን ሲሆን ሌሎች ወጪዎች ከግማሽ ፐርሰንት በላይ የሚሸፍኑ ሆነው ሳለ ሂሳቡ ወጪ ስለመደረጉ (ለምን ለምን ተግባር) የሚገልጽ ዝርዝር የወጪ/ሒሳብ ሰነድ ወይም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፡፡
- ከአጠቃላይ ከሰለጠኑት ባለሙያዎች 113 ባለሙያዎች ውስጥ 29 ሰርትፊኬት ብቻ የቀረበ መሆኑ ፡፡

105. በተጨማሪም በኢንስቲትዩቱ በኩል ከፈፃሚ እስከ አመራሩ ለሚፈጠሩ ችግሮች ፈጥኖ ምላሽ ያለመስጠት፣ ቀጣይነት ባላቸው የዘወትር ተግባራት በመጠመድ የቁርኝት ፕሮግራሙን በአግባቡ ያለመተግበር፣ የቁርኝት ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመራው የስትሪንግ ኮሚቴ በየጊዜው እና በወቅቱ እንዲሰበሰብ ሁኔታዎችን ያለማመቻቸት ክፍተቶች እንዳሉ፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና አመራሮች ለስልጠና ካላቸው የአመለካከት ውሱንነት እና በስራቸው ላይ ተተኪ ባለሙያዎችን በማግኘት ባለ ውሱንነት እና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች በቁርኝት አጋሩ እና በኢንስቲትዩቱ በሚዘጋጁ ስልጠናዎች ላይ የሰልጣኞች ተሳታፊነት ዝቅተኛ የመሆን ክፍተቶች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. እንዲሁም በIIT የቁርኝት አጋር በየአመቱ የሚዘጋጅ ሰድስት የስልጠና እና ልዩ እቅድ ማውጫ ሞጁል እንደሚዘጋጅ በስምምነት ሰነዱ የተገለጸ ቢሆንም እስከ ህዳር 2010 ድረስ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ በIIT የቁርኝት አጋር ልዩ ሞጅሎች እና አፐሊኬሽኖች ዝግጅት እንደሚከናወን የተገለጸ ቢሆንም የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፣ የIIT የቁርኝት አጋር አማካሪ

ባለሙያዎች የኢትጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ላይ በየወሩ ጉብኝት እንደሚያደርጉ ቢገለፅም ያልተከናወነ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

107. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በተቋቋመው ስትሪንግ ኮሚቴ መሰረት በየጊዜው የናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (ኒፍት) ፕሮግራም እንደሚካሄድና የኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) ፕሮግራም ግምገማ ላይ ስትሪንግ ኮሚቴው ዘገይቶ የገመገመበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም የኢንዲያን ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (አይ አይ ቲ) ህንድ የሚገኝ የትምህርት ተቋም በመሆኑ ግምገማ እንዳልተካሄደ ገልፀዋል፡፡

108. ይሁን እንጅ በኢንዲያን ኢንስቲትዩት ኦፍ ቴክኖሎጂ (አይ አይ ቲ) የስምምነት ሰነድ ላይ በአመት አንድ ጊዜ የስትሪንግ ኮሚቴው ተገናኝቶ ሊገመግም እንደሚገባው፣ በNIFT የስምምነት ሰነድ ላይ ፋብሪካዎች የቁርኝት ፕሮግራም አፈጻጸም ግምገማ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልቻልንም፡፡ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርት በስምምነት ለሁለተኛ ዲግሪ የሚማሩትን ማብዛት ይሻላል በሚል ስምምነት ተጨማሪ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲማሩበት እንደተደረገ፣ የቁርኝት ፕሮግራሙን የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን በየጊዜው እያከናወኑ መቆየታቸውን ነግር ግን በተለያዩ ምክንያቶች በሙሉዕነት አለመከናወኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅትና ለተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በሰጡት የፅሁፍ ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

109. ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር ባለመከታተሉ እና ባለመገምገሙ እንዲሁም የፕሮግራሙ ትግበራ በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት እረገድ ያመጣውን ውጤት ባለመገምገሙ፡- የዘርፉ ፋብሪካዎች ከቁርኝት ፕሮግራሙ ማግኘት የነበረባቸው አገልግሎት በአግባቡ እንዳያገኙ እና የቁርኝት አጋሩ ስራዉን በተመደበለት ጊዜ እንዳያጠናቅቅ እና ማስተላለፍ የሚገባውን እውቀት እንዳያስተላልፍ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለሥልጠና

ሙሉ ወጪ ተከፍሎ የተወሰነ ሰው ብቻ መሰልጠኑ ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

110. በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኝት ፕሮግራም፤ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ አስቀድሞ ፕሮግራሙ በኢንስቲትዩቱ ለማካሄድ የሚረዳ የተጠና የዳሰሳም ሆነ ሌላ አይነት ጥናት የሌለ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ ከህንድ ናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ (NIFT) እና ከህንድ ኢንስቲትዩት ኦፍ ኬሚካል ቴክኖሎጂ (ICT) ጋር የተፈራረመው ስምምነት ትግበራው የዘርፉን ኢንዱስትሪዎችን ማካተት እንደሚገባ ቢገልጽም እንዲካተቱ አለመደረጋቸው፡፤
- የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸውን አምራቾች ለመምረጥ የሚያስችል የተዘጋጀ መስፈርት አለመኖሩን እና በኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ቴክኖሎጂ ግብአት ሽግግር ተብለው የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች የሌሉ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም ግብአት ወደ ኢንዱስትሪዎች ለማሸጋገር ያዘጋጀው እቅድ የሌለ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር ከማሳደግ አረገድ ውስንነት የሚታይበት መሆኑ፤
- በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ እና በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የኮርስ ዝግጅት በተመለከተ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር እና

ከዩኒቨርስቲዎች ጋር መሳተፍ ባለበት በጋራ ስራዎች ላይ በሚፈለገው መጠን ያልሰራና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ያላደረገ መሆኑ፤

- በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ያላካሔደ መሆኑና መደበኛ በሆነና ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲምፖዚየም ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ወቅታዊ የሆኑ እና ቀጣይነት ያላቸው ጥናቶችን የማከናወን ውስንነት ያለ መሆኑ፤
- የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ ያልተሰራ መሆኑና የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ የሚደረገው ድጋፍ ውስንነት ያለበት መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት አጋሩ (ICT) በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያለውን የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና በመስጠት በማደግ ላይ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች እንዲደግፍ ክትትል በማድረግ እና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እረገድ ውስንነት ያለበት መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች ያላዘጋጀ እና ሥርዓተ-ትምህርቶች ያልቀረፀ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት አጋሩ (ICT) ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን እና ዘዴዎችን እንዲነድፍ ክትትል ያላደረገ እና ሁኔታዎች ያላመቻቸ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር እንዲጠናቀቅ የሚያደርገው ክትትል እና ግምገማ ከሚያዘው የግምገማ መርሃ ግብር ውጭ መሆኑና የግምገማ ኮሚቴው ኢንዱስትሪዎችን ማሳተፍ የነበረበት ቢሆንም ያላሰተፈ መሆኑ እንዲሁም የፕሮግራሙ ትግበራ በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ረገድ ያመጣውን ውጤት የማይገመገም መሆኑ፤

- ፕሮግራሙ በተያዘለት የጊዜ ገደብ NIFT ሰኔ 2010 ዓ.ም ፣ ICT ጥር 2010 ዓ.ም እና IIT ሀምሌ 2010 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን ከአጠቃላይ ከተመደበው በጀት ስራ ላይ የዋለው ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ 62.3 ከመቶ በመሆኑ ከጊዜ ገደብ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ
-

ታውቋል፡፡

111. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

112. የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር የቁርኝት ፕሮግራም፣ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መልኩ ያከናውን ዘንድ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ኢኒስቲትዩቱ ለወደፊቱ የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ አስቀድሞ ፕሮግራሙ ከመከናወኑ በፊት በዘርፉም ሆነ በኢኒስቲጥዩቱ በቁርኘት ፕሮግራም መሞላት ያለበት ክፍተትና ችግር መኖሩን የሚሳይ ጥናት ሊያከናውን እንዲሁም ፕሮግራሙ በአገር ውስጥ ባለ አቅም ሊሸፈን አለመቻሉ ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራሙ የሚገኘውን የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚተገበርባቸው በዘርፉ ላይ ከተሰማሩት የመንግስትም ሆነ የግል አምራቾች እና ተቋማት በገባው ስምምነት መሰረት ኢንዱስትሪዎቹና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያሳትፋቸው ይገባል፡፡ በፕሮግራሙንም የሚሳተፉትን ተቋማት ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ የመመረጫ መስፈርት በማዘጋጀት በመስፈርት መሰረት ሊመርጥ ይገባል፤
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት ፕሮግራም የሚገኘውን እውቀት ወደ ፋብሪካዎች በሚፈለገው ደረጃ ለማሸጋገር እና እንደየክፍተታቸውና የሙያ መስክ አንፃር ድጋፍ እንዲያገኙ የእውቀት ሽግግር ንድፈ ሀሳብ ወይም እቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤
- ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና ለቁርኝት ፕሮግራም የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ማዘጋጀት እንዲቻልና በተያዘለት የበጀት መጠንና የጊዜ ገደብ ማጠናቀቅ እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ማዘጋጀት አለበት፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ ያሉት የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የሚያፈሩት የሰው ሀይል ተግባር ተኮር እውቀት የተላበሱ እንዲሆኑ እና ፋብሪካዎችም

ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል ማግኘት እንዲችሉ በዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር የበለጠ ማሳደግ አለበት፡፡ ኢንስቲትዩቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ማሰልጠን ፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ መስራትና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ማድረግ አለበት፤

- በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማካሄድ፤ መደበኛ በሆነና ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲምፖዚየም ማዘጋጀት አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ በተመረጡ የልብስ አምራቾች በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ወቅታዊና ዘላቂነት ያለው ጥናት ማካሄድ አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ መስራትና የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ የበለጠ ድጋፍ ማድረግ አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት አጋሩ (ICT) ጋር በገባው ውል መሰረት ከቁርኝት አጋሩ ባገኘው እውቀት መሰረት በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያለውን የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና መስጠት በማደግ ላይ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች መደገፍና ክትትል ማድረግ አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች ማዘጋጀት እና ሥርዓተ-ትምህርቶች መቅረጽ አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት አጋሩ (ICT) በገባው ውል መሰረት የቁርኝት አጋሩ የውል ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን እና ዘዴዎችን እንዲነድፍ ክትትል ማድረግ እና ሁኔታዎች ማመቻቸት አለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት አጋሮቹ ጋር በገባው ስምምነት መሰረት የስምምነቱ ጊዜ ገደብ ሳይጠናቀቅ የኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት ፕሮግራም አፈፃፀም በተቀመጠው መርሃ ግብር እንዲጠናቀቅ ክትትል ማድረግ ፣ ኢንዱስትሪዎችን በፕሮግራሙ ማሳተፍ እና የፕሮግራሙ አፈጻጸም በኢንስቲትዩቱና ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ረገድ ያመጣውን ውጤት መገምገም አለበት፡፡ በተጨማሪም በስመምነቱ መሰረት ለቁርኝት አጋሮቹ ከተከፈለው አጠቃላይ ክፍያ ውስጥ ለሥልጠና የተያዘው በጀት በስምምነቱ መሰረት የሚመለከታቸው ሰዎች ሥልጠናውን እንዲያገኙ እና ሥልጥነው መጥተው ለሥራ ባልደረቦቻቸው ሆነ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት የሚያስተላልፉበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

113. በመጨረሻም ለኢንስቲትዩቱ የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ፤ በናሙና ባየናቸው የዘርፉ ኢንዱስትሪዎች ፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲትጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| ፩. ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን በቁርኝት ፕሮግራም አቅሙን በመገንባት በሰው ሀይል ልማት፣ በማማከር፣ በምርምርና ስርፀት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በጥራት ፍተሻ፣ በቴክኒክና እና በግብይት ለኢንዱስትሪዎች የሚያደርገው የድጋፍ እና የክትትል ሥራዎች አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 1. የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት ጥናት ሊከናወን ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 2. ለቁርኝቱ ፕሮግራም የሚመረጡ ተቋማት የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 3. የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበትን መስፈርት ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 4. የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች በመስፈርት ሊመረጡ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 5. ኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ፕሮግራም ግብአት ሽግግር የተመረጡትን አምራቾች ክፍተት በመለየት እቅድ አዘጋጅቶ ሊደግፍ እና የማረጋገጫ ዝርዝር አዘጋጅቶ ሊከታተልና ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 6. በዘርፉ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በረጅምና በአጭር ስልጠና ለሚሳተፉ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች የስልጠና መምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅ እና መስፈርቱ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 7. በዘርፉ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በረጅምና በአጭር ስልጠና የሚሳተፉ ባለሙያዎች በመስፈርቱ መሰረት ሊመለመሉ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ፤** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, ICT and IIT PAGE 19,13 & 5 |
| | 8. ኢንስቲትዩቱ በስምምነቱ ሰነድ መሰረት ለቁርኝት አጋሩ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችንና አገልግሎቶችን ሊያቀርብ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, ICT and IIT page 19, 13 & 5 |
| | *9.* ኢንስቲትዩቱ የሁለትዮሽ ስምምነቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ መርሃግብርና የአፈፃፀም መገምገሚያ መስፈርት ለማዘጋጀት እንዲቻል በዘርፉ አምራቾችና በቁርኝቱ አጋር መካከል የምክክር መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFIT page 19/16.4 |


| የኦዲትጭብጥ Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 10. ኢንስቲትዩቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት (በዘርፉ የሰው ሃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ) ተቋማት መካከል፤ ያለውን ግንኙነትና ትስስር ሊያሳድግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFIT page 19 |
| | 11. በቁርኝት ፕሮግራም ትግበራ በተገኘው ግብአት ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ሊያካሂድና ዉጤቱን ሊያሳትም እንዲሁም መደበኛ በሆነና ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲምፖዚየም ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, page 9 and 5 |
| | 12. ኢንስቲትዩቱ በተመረጡ የልብስ አምራቾች ውስጥ በልብስ ገበያ እና በልብስ የምርት እድገት ዙሪያ ጥናት በማካሄድ የቴክኒካል ድጋፍና የምክር አገልግሎት ሊሰጥ እና ጥናታዊ ስራዎችን ሊተገብር ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ፣** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, Page 9 |
| | 13. ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ሊደግፏቸው ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, |
| | 14. ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት አጋሩ (ICT)በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያሉትን የሰው ሀብቶች ልዩ ስልጠና በመስጠት በማደግ ላይ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች እንዲደግፍ ክትትል ሊያደርግ እና ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ፣** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and ICT, page 6 |
| | 15. ኢንስቲትዩቱ (የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) በኬሚካሎች፣ በቀለሞች እና በቴክስታይል ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ላይ የስልጠና እና የምክር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት** |
| | 16. ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ቴክኖሎጂ እና በዘርፉ አግባብነት ባለው የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኮርሶች ሊያዘጋጅና ሥርዓተ-ትምህርቶች ሊቀርፅ እንዲሁም ለአጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች የሚሆኑ ማንዋሎችን እንዲሁም ሞጁላር ኮርሶችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and NIFT, page 9 |

| የኦዲትጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
| --- | --- |
| | 17. ኢንስቲትዩቱ NIFT የተባለው አጋር ድርጅት ለዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ከልብስ ቴክኖሎጂ፣ ከግብይት፣ ከገበያ ትንተና እና ከዘርፉ የአስተሳሰብ ችሎታ (Intelligence)፣ ትንበያ (Forecasting)፣ የምርት ዕድገት ጋር ግንኙነት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ ክትትል ሊያደርግ እና ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement betweenETI ETIDI and NIFT, page 9 |
| | 18. ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት አጋሩ (ICT) ለዘርፉ ተስማሚ የሆነ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂዎችን እና ዘዴዎችን እንዲነድፍ ክትትል ሊያደርግ እና ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and ICT, page 6, |
| | 19. የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት /ኢንስቲትዩቱ በጣልቃ ገብነት የዘርፉ ልማት ለማፋጠን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ሊነድፍ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and ICT, page 6, |
| | 20. ኢንስቲትዩቱ የኬሚካል እና የአካባቢ ላቦራቶሪዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና የኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ሊያመቻችይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and ICT, page 6 |
| | 21. ኢንስቲትዩቱ (የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) በማጠናቀቂያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወደ ምርት ሂደት የተሸጋገሩና በማምረት ሂደት ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን የውስጥ አሰራራቸውን በመፈተሽ የምክር እና ቴክኒካዊ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት** |
| | 22. ኢንስቲትዩቱ (የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) በማጠናቀቂያ ስራዎች ኢንዱስትሪ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ (Quantitative & qualitative) የምርጥ ተሞክሮ ጥናት እንዲተገበር ስራዎችን ሊያስተባብር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት፣** contract agreement for twinning arrangement between ETIDI and ICT, page 6 |
| | 23. ኢንስቲትዩቱ (የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) በዘርፉ የምርት ሂደቶች ያሉትን የተለያዩ ደረጃዎችን (የግብአት፣ የምርት፣ የምርት ሂደት ቆሻሻ ፍሳሽ የመቀነሻ ስርአት፣ የተረፈ |

| የኦዲትጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
| --- | --- |
| | ምርት ደረጃዎችን) ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም ሊያዘጋጅ ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ጸድቀው ብሄራዊ ደረጃ እንዲሆኑ ሊያደርግ እና ለማጠናቀቂያ ፋብሪካዎች ሰርጸው እንዲገቡ የምክር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት** |
| | 24.ኢንስቲትዩቱ (የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) በፓተርን ሥራ፣ በፋሽን ዲዛይን፣ በቆረጣ፣ በስፌትና በማጠናቀቅ ስራዎች ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግና የፍተሻ ስራ ሊያከናውን ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት** |
| | 25.ኢንስቲትዩቱ (የጋርመንት ቴክኖሎጂሽ ዳይሬክቶሬት) የአልባሳት ኢንዱስትሪዎች የጥራት ደረጃቸውን በማሻሻል በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠበቁ እና የመሳሰሉ የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት እንዲችሉ በሙያ መስኩ መተግበር ስለሚገባቸው ሁኔታዎች የምክር አገልግሎት እና የስልጠና ድጋፍ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬትዝርዝር ተግባራት** |
| | 26.ኢንስቲትዩቱ (የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ሊያሰለጥን፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ ሊሰራና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ተግባራት** |
| | 27.ኢንስቲትዩቱ የቁርኝት መርሀ-ግብሩን አፈፃፀም በየጊዜው በመከታተል በየሶስት ወሩ ሪፖርት በማዘጋጀት ሊገመግም እና የቁርኝት ትግበራው በኢንስቲትዩቱና በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ልማት እና አቅም በመገንባት ያመጣውን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡<br>**ምንጭ የ2008 በጀት አመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና (2008-2012 ስትራቴጂክ እቅድ)** |
| | 28.ኢንስቲትዩቱ የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የዘርፍን ልማት ሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የምርት ሂደት፣ የምርት ዕቅድ፣ የጥራት ቁጥጥር እና የስራ አመራር የሥልጠና ድጋፍና የማማከር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ የጨርቃጨርቅ እንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 39** |
| | *29.*ኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ ተመራማሪዎች፣ ተማሪዎች እና ሰልጣኞች ለምርምር እና የተግባር ስራዎች አገልግሎት የሚውሉ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች እና ግብአቶች በሚፈለገው ሁኔታ ሊያሟላ ይገባል፡፡ |

| የኦዲትጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
| --- | --- |
| | **ምንጭ፡- ኢንስቲቱዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር መመሪያ ጥናት** |
| | 30. ኢንስቲትዩቱ የስፌት ፋብሪካዎች ላይ የምርጥ ተሞክሮ ትግበራ እንዲካሄድ ማድረግ፣ በዋጋ እና በጥራት ተወዳዳሪ ምርቶችን በማምረት የኤክስፖርት ገቢ እንዲጨምር ለማስቻል ሊከታተል ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ የኢኒስትቱዩቱ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር እቅድ 2008-2012 ገፅ 66** |
| | 31. ኢንስቲትዩቱ ዕውቅና ያላቸው ዓለም ዓቀፍ የዘርፉ ምርት ገዥና ቸርቻሪ የሆኑት ብራንድ ኩባንያዎችን ማዕከል ያደረገ የገበያ ድጋፍ በማድረግ የወጪ ንግዱን ሊያጠናክር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የሁለተኛው አምስት ዓመት (2008-2012) የጥጥ ልማተና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ገጽ 36 እና 37** |
| | 32. ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ላይ የሚታየውን የሃይል ብክነት እና የሚለቁትን የካርበን መጠን እንዲቀንሱ በማድረግ የአካባቢ ጥበቃን ዘለቄታዊ ያለው መፍትሄ እንዲያገኝ በማድረግ ኢኒስቲትዩቱ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የሁለተኛው አምስትዓመት (2008-2012) የጥጥ ልማተና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ገጽ 36 እና 37** |
| | 33. ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ሊሰራ እንዲሁም በጋራ የምርምር ሥራዎችን ሊያካሂድ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ የጨርቃጨርቅ እንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ** |
| | 34. ኢንስቲትዩቱ ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣በ ማደራጀት፣ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ እና የዘርፉን አቅም ሊያሳድግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ የጨርቃጨርቅ እንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 39** |

# አባሪ 2፡ የኢነስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 3፡ የኢኒስቲትዩቱ የሚሰጣቸው ድጋፍና አገልግሎቶች

## በኢንስቲትዩቱ የጨርቃጨርቅ ልማት ዘርፍ ሥር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡዋቸው ድጋፍና አገልግሎቶች

<u>**የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት**</u>

- ❖ በዘርፉ ያሉትን የሥራ ሂደት መረጃዎችን መሰብሰብ፣ማጠናቀርና ወቅታዊ ማድረግ፤
- ❖ በዘርፉ ለፋብሪካዎች የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እንዲሁም የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ❖ በዘርፉ ለፋብሪካዎች የቤንችማርኪንግ የዳሰሳ ጥናት፣ የክፍተት ዳሰሳ ጥናት እና በክፍተት ዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሰረተ የቤንችማርኪንግ ትግበራ ማከናወን፤
- ❖ በዘርፉ ለፋብሪካዎች ችግር ፈቺ፣ ጥራትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ጥናቶች እና የምርምርና ስርፀት ሥራዎችን ማከናወን፤
- ❖ በዘርፉ ለፋብሪካዎች በምርታማነት፣ በጥራት፣ በምርት ሂደት ባሉ ብክነቶች እና በአመራረት ሥራ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች የማማከርና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
- ❖ ከምርምር ላብራቶሪ ዳይሬክቶሬትና ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የጥጥ፣ የፈትል ምርት ሂደት ቅድመ ምርቶች እና የክር ምርት ደረጃዎችን ማውጣት፤
- ❖ ከኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር በጥጥ መዳመጫ እና ፈትል ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ የሚሆን የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀት፣ የአዋጪነት ጥናት ማከናወን፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ ድርድር፣ ተከላና ድጋፍና አገልግሎት መስጠት፤
- ❖ ከግብይት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የግብዓትና ምርት ትስስር በጥጥ አምራቾች፣ በጥጥ መዳመጫዎችና በፈትል ፋብሪካዎች መካከል እንዲፈጠር መከታተልና መደገፍ፤

<u>**የሽመናና ሹራብ ሥራ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት**</u>

- ❖ የንዑስ ዘርፉን መረጃ በማጠናከር ለተጠቃሚዎች ማድረስ
- ❖ በዘርፉ ስልጠና መስጠት
- ❖ ምርጥ ተሞክሮ ትግበራ መፈጸም
- ❖ የቴክኒክ ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት
- ❖ በዘርፉ የምርምርና ስርፀት ስራ ማከናወን
- ❖ የሽመናና ሹራብ ሥራ ክፍል ፋሲሊቲዎችን ማሟላት

እነሱም፡-

<u>የሹራብ ሥራ ወርክሾፕ</u>

<u>የሽመና ወርክሾፕ</u>

**<u>የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት</u>**

- ❖ በኬሚካሎች፣በቀለሞች እና በቴክስታይል ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ላይ ስልጠና ይሰጣል፣ያማክራል፤
- ❖ የጨርቃጨርቅ ማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ በዘርፉ ዓለም በደረሰበት ደረጃ ሊያደርስ የሚያስችሉ ጥናቶችንና የምርምር ተግባራትን ያከናውናል፤
- ❖ በማጠናቀቂያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወደ ምርት ሂደት የተሸጋገሩና በማምረት ሂደት ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን የውስጥ አሰራራቸውን በመፈተሽ ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ❖ የማጠናቀቂያ ኢንዱስትሪ የስራ መስክን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሞዴል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፤
- ❖ በማጠናቀቂያ ስራዎች ኢንዱስትሪ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ (Quantitative & qualitative) የቤንችማርኪንግ ጥናት እንዲተገበር ስራዎን ያስተባብራል፣በጋራ ይሠራል፤
- ❖ በማጠናቀቂያ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተሟላ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችላቸውን መመሪያ ያዘጋጃል፣ከግብዓት እስከ የተለያየ የገበያ ፍላጎት ደረጃ ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀ ምርት ድረስ ባሉት ሂደቶች ያሉትን የተለያዩ ደረጃዎችን ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም ያዘጋጃል፣
- ❖ የጨርቃጨርቅ ማጠናቀቂያ ኢንዱስትሪ የፕሮጀክት ጥናት አገልግሎት (የማጠናቀቂያ ፋብሪካዎችን አስተማማኝ ለማድረግ የመሳሪያ መረጣ፣የመሳሪያ ተከላ ድጋፍ እና የኮሚኒኬሽን ድጋፍ ይሰጣል በማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ላይ የተዘጋጀውን ደረጃ በብሄራዊ ደረጃ ያፀድቃል፣የማስረፅ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፣
- ❖ በዘርፉ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እንዲሁም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
- ❖ በማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ የደንበኛና የምርምርና ምርት ልማት ጥያቄ ይቀበላል፣የምርምርና ምርት ልማት ናሙና (ፕሮቶታይፕ) ዲዛይን በመገምገም ይወስናል፡፡

**<u>የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት</u>**

- የጋርመንት ኢንዱስትሪዎችን ችግሮች የሚፈታ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወንና ውጤቶችን በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች በማስተላለፍ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በዘርፉ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት፤
- በዘርፉ የተለያዩ የምርት ማሻሻያ ዘዴዎች እና የስራ ልኬቶች በማከናወን የቴክኒክ ድጋፎች ማድረግ፤
- የፓተርን ሥራ፣ የፋሺን ዲዛይን፣ ቆረጣ፣ ስፌት፣ ማጠናቀቅ እና ግብይት ስራዎችን ዓለምአቀፍ ምርጥ ተሞክሮ የደረሰበት ላይ ሊያደርስ የሚያስችል የቤንችማርኪንግ ሥራዎችን ማከናወን፤
- በፓተርን ሥራ፣ በፋሽን ዲዛይን፣ በቆረጣ፣ በስፌትና በማጠናቀቅ ስራዎች ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግና የኢንስፔክሽን ስራ ማከናወን፣
- የአልባሳት ኢንዱስትሪዎች የጥራት ደረጃቸውን በማሻሻል በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠበቁ እና የመሳሰሉ የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት እንዲችሉ በሙያ መስኩ መተግበር ስለሚገባቸው ሁኔታዎች የምክር አገልግሎት፣ የስልጠናና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ
- በጋርመንት ኢንዱስትሪ ዘርፍ እና ከቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት የቴክኒክ መረጃዎች ማሰባሰብና ወቅታዊ ማድረግ፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ማሰልጠን ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ በመስራትና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ማድረግ
- ከኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን በጋርመንት ኢንዱስትሪው ለሚከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም ክትትል ማድረግ፤
- ከግብይት ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን የጋርመንት ኢንዱስትሪዎች ዓለም አቀፍ ገበያቸው እንዲረጋገጥ በስራ ሂደቱ በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራት፤
- በዳይሬክቶሬቱ በተሰጠው ድጋፍ ተጠቃሚዎች ያገኙትን ውጤት መገምገም፣ ክፍተት ካለ መለየትና መሙላት፣በዘርፉ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን መደገፍና ማፍራት፣

## በኢንስቲትዩቱ የቴክኒክ ዘርፍ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡአቸው ድጋፍና አገልግሎቶች

<u>**የምርምር ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት**</u>

- በጨርቃጨርቅ ምርት እና ግብዓቶች ላይ የሚሰጥ የጥራት ፍተሻና በጭረት ላይ የሚሰጡ ፍተሻዎችን መከወን
- በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ፍተሻ ላብራቶር ላይ ድጋፎችን መስጠት
- በላብራቶር ውስጥ የሚገኙ የጥራት ፍተሻ መሳሪያዎችን ማሟላት፣ አሁን ላይ ያሉት የላብራቶር መሳሪያዎች

  -የኢንቫይሮሜንታል ላብራቶር

  -የፊዚካል ላብራቶር

  -የኬሚካል ላብራቶር

<u>**የኢንጅነሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ኢነርጂ ዳይሬክቶሬት**</u>

- የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንቨስትመንትን ማሳደግ
- የኢንጂነሪንግ አቅምን ማሳደግ

<u>**የጥጥ እና ጨርቃጨርቅ ግብይት ዳይሬክቶሬት**</u>

- የገበያ መዳራሻን ማስፋት
- የግብዓት አቅርቦትን ማረጋገጥ
- የኢምፖርት ኤክስፖርት የስራ ሂደትን ማሳለጥ
- የገበያ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን
- በጥጥ እና ጨርቃጨርቅና ስፌት ስራ ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎቻችን ለገበያ ውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን ሰብስቦ በማደራጀት እና በመተንተን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣
- የጥጥ ክምችት ስርዓት እና የጥጥ ግብይት በዘመናዊ መንገድ እንዲመራ ተፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን ማረጋገጥ፣

<u>**የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስልጠና ዳይሬክቶሬት**</u>

- የዩኒቨርስቲ፣የቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት እና የጨርቃጨርቅ ልማት ዘርፍ ኢንዱስትሪዎች ትስስር አጠቃላይ እንቅስቃሴውን ማስተሳሰር፣
- የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማትን ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የሚደረግ ትስስርን ማስተባበር፣
- የሙያ ብቃት ምዘናን ማስተባበርና መደገፍ፣
- ትምህርቱንና ስልጠናውን ላጠናቀቁ ሰራተኞች የምስክር ወረቀት ማዘጋጀት፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት መምህራን የአሰልጣኞች የስልጠና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ማስተባበር፣

- አጠቃላይ የተቋሙን ምርምርና ስርፀት ማስተባበር፣

## በኢንስቲትዩቱ የጥጥ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚሰጡአቸው ድጋፍና አገልግሎቶች

**<u>የጥጥ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት</u>**

- የጥጥ ጥራት ደረጃዎች እንዲዘጋጁ /የተዘጋጁት እንዲሻሻሉ ማድረግ
- በጥጥ/ጭራ/ ባህሪያት ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ
- በጥጥ ጥራት ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት
- የጥጥ ግብይት ጥራትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- በጥጥ ጥራት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት
- በላቦራቶሪ የፍተሻ ውጤት መሰረት የጥጥ ጥራት ውጤትን መተንተንና መገምገም
- የጥራት ፖሊሲን መገንባትና ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት
- የጥጥ ምርት የአካባቢ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ግንዛቤ መፍጠር

**<u>የጥጥ ልማት ዳይሬክቶሬት</u>**

- የጥጥ ምርት ምርታማነትና ጥራቱን ሊያሳድጉ የሚችሉ ስራዎች እንዲከናወኑ የሙያ ምክርና ድጋፍ መስጠት፤
- ለጥጥ ልማት ጠቃሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እንዲባዙና እንዲሰራጩ ድጋፍ ማድረግ፤የሙያ ምክር መስጠት፣
- በጥጥ ልማት ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል ለማብቃት የሚያስችል ስልጠና መስጠት፣
- ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የጥጥ ሰብል ምርምርና ስርጸት ስራዎችን ማከናወን፣
- የጥጥ ልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ማስተባበር፤አፈጻጸማቸውን መከታተል፣
- የጥጥ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን እና ተሞክሮዎችን በመቀመር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በመስኖ የሚለሙ የጥጥ እርሻዎችን ማስፋፋትና ድጋፍ መስጠት፣
- ለጥጥ ሰብል ልማትና፣ተባይና በሽታዎች ለመቆጣጠር የሚረዱ ማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤
- የጥጥ እርሻ ሊለማባቸው የሚችሉ መሬቶችን መለየት

- ለጥጥ አልሚ ባለሀብቶች የፋይናንስ አቅርቦትን እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ፣
- ወደ ጥጥ ልማት ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት መረጃ፤የሙያ ምክር፤ክትትልና ድጋፍ መስጠት፤
- ለጥጥ ልማቱ ግብዓት የሚሆኑ ቁሳቁሶችና ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ድጋፍ መስጠት፣
- የኦርጋኒክ ጥጥ ምርትን የሚያረጋግጥ አካል እንዲቋቋም ማድረግና በጋራ መስራት፣
- ጥጥ አልሚ አርሶ አደሩ ወደ ኮንትራት ኦርጋኒክ የጥጥ ልማት እንዲገቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- ለጥጥ ልማቱ ድጋፍ የሚያደርጉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በጋራ መስራት

## አባሪ 4

# ለናሙና የተመረጡ የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትት ተቋማት፡-

| ተ.ቁ | የፋብሪካዎች ስም |
|---|---|
| | በICT የቁርኝት ፕሮግራም ድጋፍ ያገኙ ፋብሪካዎች |
| 1. | ቪሌጅ እንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ |
| 2. | ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ |
| 3. | ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ |
| 4. | ዲኤች ገዳ የአክሪላክ ማቅለሚያ ፋብሪካ |
| 5. | አልመሂዲ እንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ) |
| | በNIFT የቁርኝት ፕሮግራም ተደራሽ የተደረጉ ፋብሪካዎች |
| 6. | ይርጋ አለም አዲስ ጨርቃጨርቅ እንዱስትሪ |
| 7 | ደስታ ጋርመንት |
| 8 | ኤልቴክስ የጨርቃጨርቅ እና ጋርመንት እንዱስትሪ |
| 9 | ኖቫስተር ጋርመንት ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ |

**ዩኒቨርሲቲዎች**

1. ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
2. በወሎ ዩኒቨርሲቲ ኮምቦልቻ ካምፓስ

- **የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት**

1. ባህርዳር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
2. ኮምቦልቻ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

# አባሪ 5

NIFT

- The scope of responsibilities of the twinning partner shall be capacity building of TIDI and providing services to the industry which includes the following activities (NIFT, page 6 of 11):
  - Provide training on maintenance of machineries for TIDI staff and to the industry ( NIFT,page 7 of 11,# 5)
  - Provide technical support in all the spheres of garment sector (NIFT, page 7 of 11,# 8)
  - Provide services to the industry such as testing, certification and establishing norms and standards (NIFT, page 7 of 11, #9)
  - Follow up and audit the performance of the companies and propose/take corrective actions (NIFT, page 7 of 11,# 15)
  - Identify key areas of intervention for making the garment sector globally competitive in terms of fulfilling compliance requirements (NIFT, page 7 of 11, # 12)
  - Forecasting the global market dynamics and preparing the Ethiopian textile and garment sector products to meet the changing requirements (NIFT, page 7 of 11. # 14)
  - it shall facilitate consultation meeting between the identified beneficiary Apparel manufacturing companies and the experts from Twinning Partner to prepare mutually agreeable beneficiary oriented Action Plan and norms for performance evaluation (NIFT, page 19 of 26)
  - and to design and put in place systems for promoting, interactions and linkages with the industry , TIDI, TVETs and/or institutions of higher learning for human resource development , research , and technology transfer (NIFT, page 9 of 26,ii)
  - providing technical support and conducting research activities in Apparel Manufacturing, Marketing and Product development through

two joint research in selected areas and providing technical support and Consultancy services through two joint consultancy in selected areas (NIFT, page 9 of 26, 6.4 & 6.5

ICT

❖ The specific objectives of the proposed project ( the ICT and ETIDI twinning program) are ( ICT, page 5 of 21, # 5.3)

- Provide training on maintenance of machineries for finishing technology directorate staff and to the industry ( ICT, page 5 of 21)
- Build up the networking and outreach program of finishing technology directorate for the provision of its services to the industries on a sustained basis and also provide all relevant training to the industry personnel (ICT, page 5 of 21)
- Provide services to the industry such as testing, certification and establishing norms and standards (ICT, page 5 of 21)
- Identify key areas of intervention for making the Textile Processing sctor globally competitive in terms of fulfilling compliance requirements (ICT, page 5 of 21)
- Develop support packages , which will strengthen strategically the competitive advantage of the Ethiopian Textile Processing sector (ICT, page 5 of 21)
- Support the industry in developing its human resources at managerial, technical and skilled work force levels by providing specialized training (ICT, page 5 of 21)
- Implement benchmarking at company level and also monitor bench marking implementation by other consulting firms in collaboration with the industry (ICT, page 5 of 21)
- Develop an information support system to collect, analyze, organize and disseminate information that will enhance the development of the sector (ICT, page 5 of 21)

- Upgrade the capability of providing consultancy and technical services to improve the quality and quantity of textile processing industry products (ICT, page 5 of 21)

- Introduce and Implement tripartite linkage system among the Industry, ETIDI, higher institutions and TVET for human resource development, research, technology transfer etc. (ICT page 6 of 21)

Office of the Federal Auditor General